# የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች

እንጸልይ።

ጌታ ሆይ፡ አሁን እናምናለን። በእግዚአብሔር ልጅ እናምናለን፡ እናም፡ በዚህም፡ የዘላለም ህይወትን በእርሱ በኩል እንቀበላለን። ለመልእክቱ እና ዛሬ ማታ፡ ለምትነግረን ነገር፡ በአንተ በማመን፡ ዛሬ ከሰአት፡ ወይም ማታ፡ አሁን እንደገና ለሌላ አገልግሎት ተሰብስበናል። ጌታ ሆይ እናምንሃለን፡ አንተንም እንጠብቃለን። አንተም እንዳልከው፡ "እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፡ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ።" እኛም አንተን በምንጠብቅበት፡ በዚህ ምሽት፡ ያን ኃይል-ጨማሪውን እንድትሰጠን፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እንጸልያለን።

2 ለአንተም ስላላቸው ለእኔም ስላላቸው ትርጉም፡ ስለ እነዚህ ሰዎችም እናመሰግንሃለን። አባት ሆይ፡ ስለዚህም አመሰግንሃለሁ። ዕንቁዎችህ ናቸውና። እግዚአብሔር ሆይ፡ በዚህ ምሽት፡ በሚያስፈልጋቸው መንገድ፡ ራስህን፡ እንድትገለጥላቸው፡ እጸልያለሁ። የታመሙ ካሉ፡ ይፈወሱ። በአንድ ሰው አእምሮ ውስጥ ጥርጣሬ ካለ፡ አጽዳው፡ ጌታ ሆይ። ያስፈልጉናልና፡ መገኘትህን እና በረከቶችህን ስጠን። ጌታ ሆይ፡ አንተ በነገር ሁሉ-ብቃታችን ነህ። እናም፡ ያለ አንተ፡ ምንም ማድረግ አንችልም።

3 ላደረክልን ነገር ሁሉ ምስጋናችንን እንድትቀበል እንጸልያለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በረከቶችህንን እንጠባበቃለን። አሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

4 መልካም፡ ባለፈው እሁድ ምሽት፡ ከነበረው ይልቅ፡ በዚህ እሁድ ምሽት፡ እዚህ ውስጥ—ትንሽ ይቀዘቅዛል። ይህንን ለማድረግ በታማኝነት የሰሩትን ወንድሞቻችንን በጣም እናመሰግናለን። ከእነርሱ ውስጥ ሁለቱን ወይም ሶስቱን አውቃችኋለው። ከኋላ እንደማየው፡ ወንድም ማይክ ኢጋን፡ ወንድም ማይክ፡ እና ወንድም... ሶትማን፡ ወንድም ሮይ ሮበርሰን፡ (ይመስለኛል) በተጨማሪም ወንድም ዉድ፡ እና ሁሉም፡ ይህን መልዕክት ዛሬ፡ ወይም አሁን እንዲኖረን ለማድረግ፡ በብዙ ልፋት ሲሰሩ ቆይተዋል። ስለዚህ፡ እኛ አመስጋኞች ነን።

5 አሁን፡ በሚቀጥለው እሁድ ጠዋት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ለታመሙት የፈውስ አገልግሎት ጸሎት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ። እናም ጌታ ቢፈቅድ፡ ለፈውስ አገልግሎት እናውለዋለን።

6 ዛሬ ጠዋት፡ እዚህ ብዙ መሀረቦች እንዳሉ፡ አስተውያለሁ። ጸልየባቸዋለሁ። እናንተ ስትጸልዩና ስትዘምሩ፡ መሃረቦች ላይ፡ ጸልዬአለሁ፡ ዛሬ ማታም ብዙ ተጨማሪ እዚህ አለ። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር የታመሙትን እንደሚፈውስ እ—እናምናለን። በጣም ብዙ ታላላቅ የፈውስ ምስክርነቶች በመካከላችን፡ እና በመላው አለም አሉን፡ ለዚህም እናመሰግናለን።

7 በሚቀጥለው እሁድም፡ ትንሽ ዞር ዞር ማለት እንዳለብኝ፡ ተሰምቶኛል፡ እኛም ትምህርቱንና መልእክቱን ብቻ አጥብቀን ይዘን ቆይተናል፡ የፈውስ

አገልግሎት፡ ለታመሙ ሰዎች የምንጸልይበት ቢኖረን—ጥሩ ነገር ነው ብዬ አስቤአለሁ። እግዚአብሔር ድንቅ ጊዜ እንደሚሰጠንም እናምናለን።

8 አሁን፡ አብዛኞቻችሁ ዛሬ ማታ ብዙ ርቀቶችን መንዳት ይጠበቅባችኋል። እና ዛሬ እራት በበላሁበት በ—በብሉ ቦር ካፌቴሪያ፡ በዛ ካሉ ሰዎች ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። ከዚህ በፊት የማላውቃቸው ሰዎች፡ ወደዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን፡ ብዙ ጥሩ ሰዎችን፡ እጃቸውን እየጨበጥኩ የማነጋገር እድል አግኝቼ ነበር። እና ስለ እንደ እነዚህ አይነት ወዳጆች አመሰግናለሁ፡ እና እያንዳንዳችሁን ሁላችሁንም ማመስገን እፈልጋለሁ። አንዳንዶቹ ጥቁር እንጆሪዎችን ለቅመው፡ አመጡልን። እና አንዱ ባልዲ ሙሉ ጣፋጭ መጠጥ፡ ወይም ሞላሰስ፡ የመሳሰሉ ነገሮች፡ ይመስለኛል—ይዞልን መጣ። ያ ምን ማለት እንደሆነ አታውቁም። የሆነ ጊዜ ላይ... በማለዳ ተነስቼ፡ ከቤት ወጣሁ፡

9 ባለፈው ቀን ጠዋት አንድ ወንድም በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ ነበርና፡ ልብሶችም ሌሎች ነገሮችም አልነበሩትም፡ ሄጄ ልብስ እንዳመጣለት ፈልጎኝ ነበር። ልወጣ ስል፡ እነሆ ጥቁር እንጆሪ የሞላ ባልዲ ፊት ለፊቴ አስተዋልኩ። እኔም እንዲህ አልኩት፡ "እነዚህን ጥቁር እንጆሪዎችን ያመጣሃቸው አንተ ነህ? "

10 እርሱም "አይ፡ በጭራሽ እኔ አይደለሁም። ከጧት ጀንበር በፊት ጀምሬ እዚህ ነኝ፡ ያኔም እዚህ ተቀምጠው ነበር፡" አለኝ። እና መልካም ወንድሜ ሩዴል ነው ያመጣልኝ። ስለ፡ እነዚህም ነገሮችም፡ በእውነት አመሰግናለሁ።

11 ቢሊ ፖል፡ ቀደም ብሎ ጥቅሶልኝ ነበር፡ ዛሬ ማታ በጉባኤው የሚገኙ አንዳንዶች፡ ሰጦታ እንዳመጡልኝ ነገረኝ፡ ለዚህም—አመሰግናለሁ። ያን እንድታደርጉ፡ አልፈለኩም። ስለ—ጥረታችሁ፡ እና ስለ ሌላው ሁሉ አመሰግናለሁ፡ ግን ያ አስፈላጊ አልነበረም። እና፡ ግን፡ ጌታ ይባርካችሁ። ታውቃላችሁ፡ ታውቃላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "ከእነዚህ ከሁሉ ለሚያንሱት ያደረጋችሁትን፡ ለእኔ አደረጋችሁት።"

12 አሁን፡ በመልእክቱ ላይ፡ በጣም በቀጥታ፡ እያናገርኳችሁ ቆይቻለሁ። ምናልባት እ... አንዳንድ ሰዎችም እንዲህ አይነት ያሰባሉ ማለት—በአሳቤ ኢየሱስ ማለዳ ወይም ዛሬ ማታ ይመጣል እንደሆነ ያሰባሉ። አዎን እንደዚያው ነኝ። ግን፡ እንዲሁ ይሆናል አላልኩም። እና፡ ለሚቀጥለው ሳምንት ላይመጣም፡ ይችላል፡ በሚቀጥለውም ዓመት ሊሆን ይችላል፡ በአሥር ዓመታት ሊሆን ይችላል። መቼ እንደሚመጣ አላውቅም። ነገር ግን፡ አንድ የምፈልገው ነገር አለ... ሁል ጊዜ አስተውሉ፡ በየደቂቃው ወይም በየሰዓቱ ተዘጋጁ። እያችሁ? ማለት፡ ዛሬ ካልመጣ፡ ነገ ሊመጣ ይችላል። ብቻ እየመጣ እንደሆነ፡ አትርሱ።

13 በምድር ላይ የመጨረሻ ሰዓቴ በየትኛው ሰዓት እንደሚሆን አላውቅም፡ ማናችንም አናውቅም። ማናችንም ብንሆን መቼ እንደሚመጣ አናውቅም። እሱ ራሱ፡ እንኳን አያውቅም፡ በገዛ ቃሉ እንደተናገረው፤ "መቼ እንደሚመጣ፡ የሚያውቀው፡ አብ ብቻ ነው፡ወልድም እንኳን መቼ እንደሚመጣ አያውቅም፡" ብሏል። ያ የሚሆነው እግዚአብሔር እርሱን ወደ እኛ ዳግመኛ ሲልከው ነው። እኛ ግን የእርሱን መምጣት እየተጠባበቅን ነው። እና በእኔ ትውልድ ውስጥ ካልመጣ፡ በሚቀጥለው ውስጥ ሊመጣ ይችላል፤ በዚያኛውም ካልመጣ፡ በሚቀጥለው ይመጣል። ነገር ግን፡ ለራሴ ግን፡ የቀረኝ ጊዜ እንዳለ አይታየኝም። እንደው ለ... እኔ፡ በማንኛውም ደቂቃ ውስጥ ሊሆን ይችላል። አሁን፡ ይህ

ማለት ግን... እንግዲህ፡ እንዲህ አይደለም፡ ማለት ሰማያት ሲቀየሩ እና ሁሉንም ነገር ታያላችሁ ማለት አይደለም... እኔ የማወራው ስለ መምጣት አይደለም፡ ስለ መነጠቅ ነው።

14 እያችሁ፡ ሦስት አይነት አመጣጥ ያደርጋል። የመጣው በሶስት የልጅ ሰሞች ነው። በሦስትነት መጣ፡ አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ። እያችሁ፡ ይህ ሁሉ፡ ሁሌም አንዱ ክርስቶስ ነው፡ አንድ አምላክ። እንግዲህ፡ የመጣው ሦስት የጸጋ ስራዎችን ለማምጣት እንደሆነ እናውቃለን፡ ጽድቅ፡ ቅድስና፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት። በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ነገር ሁሉ፡ በሦስት ይጠናቀቃል።

15 ስለዚህ፡ በመጀመሪያ፡ ሙሽሪቷን ሊቤዣት መጣ። በሁለተኛ ደረጃ፡ ሲመጣ፡ ሙሽሪቷን ለመውሰድ፡ በንጥቀት ይመጣል። በሦስተኛ፡ ከሙሽሪት ጋር፡ እንደ ንጉሥ እና ንግሥት፡ ይመጣል፡ ያ የሚሆነው ብዙ ሰዎች፡ መምጫውን ሰጠብቁ ነው።

በዚህ ጊዜ ሲመጣ ግን፡ መቼ እንደሚመጣ ከተዘጋጁት በቀር ማንም አያውቅም። የሰዎች መሰወር ይከሰታል። ምን እንደደረሰባቸው አይታወቅም። በቅጽበት፡ ወዲያውኑ ይነጠቃሉ፡ ከዚያ በኋላም ይታጣሉ። "በቅጽበት ዐይን፡ ይለወጣሉ።" ስለዚያም የተዘጋጃችሁ ሁኑ። አንዴ የሚወዱትን ሰው በጀምበር ማጣት አስከፊ ይሆናል፡ ማንም ሊያገኛቸው አይችልም። መፈጸሙን ማወቁ እና እንዳመለጣችሁ ማወቃችሁ እጅግ አያስከፋም ወይ? ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ተጠበቁ።

16 አሁን፡ በሚቀጥለው ሳምንት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው ሰኞ፡ ከዚህ ሰኞ ሳምንት ጀምሮ፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ቤተሰቤን ትምህርት ቤት ወደሚሄዱበት ወደ አሪዞና እየወሰድኳቸው ነው፡ ከዚያ ተመልሼም እ— እመጣለሁ።

17 አሁን፡ ወደዚያ ወጥቼ አልሄድም... እኔ እዚያ የምካፈለው ምንም አይነት አገልግሎት የለኝም። እኔ በአሪዞና እምብዛም ነኝ። ሌላ ቦታ እሄዳለሁ እንጂ። በሚቀጥለው ሰኞ፡ ሚስቴን ወደዚያ እወስዳታለው። እንደገና ወደዚህ እመለሳለሁ። ከዚህ ወደ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ እሄዳለሁ። ወደ ኮሎራዶ እመለሳለሁ። በገና አካባቢ የሆነ ጊዜ እንደገና አሪዞና እሆናለሁ፡ ቤተሰቤን አንድ ላይ ለማግኘት፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፡ በቂ ጊዜ... ምናልባት፡ ሁለት ወይም ሶስት ቀናት፡ በገና በዓላት ወደዚህ እመለሳለው፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ እዚህ በአዲሱ ዓመት ሳምንት አገልግሎት ይኖረናል።

18 ስለዚህ እኔ፡ በተግባር፡ የበለጠ እዚህ ነኝ። እዚያ ከምሆነው ይልቅ አሰር እጥፍ እዚሁ ነኝ፡ ምክንያቱም በዚያ ምንም ቤተ ክርስቲያን ወይም ምንም አገልግሎት የለንም። ማለቴ፡ በዚያ አካባቢ፡ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ዙሪያ ምንም ነገር የለንም። መጥፎ ጎኑ ያ ነው። ልጆቻችሁ እዚህ እንደሚሰሙት ሁሉ፡ መልእክቱን እንዲሰሙ ልጆቼን የምልክበት ቦታ የለኝም፡ ስለዚህ— አንድ ጉድለታችን ያ ነው። ግን ሁሉም በጣም ጤናማ ናቸው። ደረቅ፡ ሞቃታማ፡ ደረቅ የአየር ጠባይ ቢሆንም፡ ልጆች ሁሉ ግን ጤናማዎች ይመስላሉ። እኔ ጤናማ መሆኑን እና አለመሆኑን ለማወቅ በቂ ጊዜ የለኝም። እኔ፡ በእንቅስቃሴ ላይ ነኝ፡ እና ተጓዥ ሆኜ እንደተወለድኩ እ—እ—እሰባለሁ።

19 ሚስቴ ትደውልልኛለች... እዚ እንደሆነች አውቃለው፡ ሁላችሁ እንደምታውቁት፡ ከቤተ ክርስቲያን በኋላ ይህን አደርጋለሁ። ምንድን ነው የሚባለው፡ የሚቀያየሩ ንፋሶች፡ ወይም እረፍት ይሌላቸው ንፋሶች፡ ወይም ምንምይሁን—ምንም፡ የሚቀያይር አሽዋ፡ ታውቃላችሁ? ወይም፡ በሌላ ቋንቋ፡ ዘወትር በጉዞ ላይ። ካገባው አሁን፡ ሃያ-ሁለት አመት ሆኖኛል፡ እንደው መሄድ ስላለብኝ፡ እኔም፡ አንዳንዴ፡ እቤት ውስጥ እንግዳ እንደሆንኩ አስባለው።

ግን አንድ ቀን አገር ቤት የምንቀመጥበትን ጊዜ እናፍቃለሁ። ለአሁን ግን ጦርነቱ ተጀምሯል፡ ስለዚህ እንጸልይ።

20 እንዳትረሱ፡ ቀጣይ እሁድ ጠዋት፡ እንደ ጌታ ፍቃድ፡ የታመሙትን እና የተቸገሩትን ይዛችሁ ኑ። ቀደም ብላችሁ ኑ፡ የጸሎት ካርዶችን መስጠት አለብን። ቦታችሁን ያዙ፡ እና ምናልባት የሚጸለይለት ቡድን ሊኖር ይችላል። በቂ ካልሆነ፡ የጸሎት ካርዶችን አንሰጥም፡ ብዛቱ ሶስት ወይም ሁለት የሆነ፡ መስመር ለመመስረት በቂ ነው። ነገር ግን—እኛ የጸሎት ካርዶቹን ልንሰጣችሁ እንችላለን፡ ምናልባት መደበኛ ፕሮግራም ከመጀመሩ ከአንድ ሰአት በፊት ልናደርገው እንችላለን፡ እንደሚፈጅ አገምታለሁ... በሰምንት ሰአት፡ ሰምንት፡ ወይም ሰምንት-ተኩል፡ ላይ ካርዶቹን ይሰጣሉ፣ ቤተክርስትያንን ይከፍታሉ፡ በቀጣይ ሳምንት እሁድ የጸሎት ካርዶቹን ይሰጣሉ። እዚህ እንደምትገኙ እርግጠኞች ሁኑ፡ የምትወዱትንም ሰው ይዛቹ ኑ፡ እዚያ አስገቧቸው። በበተክርስቲያን ውስጥ ጥሩ እና መልካም ይሆናል፡ የታመሙ ከሆነ፡ ለእነርሱ ለመጸለይ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን።

21 በድጋሜ፡ ላሳያችሁኝ ፍቅር፡ አመሰግናለሁ።

22 አሁንም ዛሬ ማታ፡ ከእግዚአብሄር ቃል ከፍለን እናነባለን፡ ቃሉንም እንዲያመጣልን ለህልውናው ዝግጁ ሁኑ። ማለት፡ ሁላችንም ጥቅሱን ማንበብ እንችላለን፡ አንቀጹን ማብራራት የሚችል ግን እግዚአብሔር ነው። አያችሁ? ጥቅሱን ልናነበው እንችላለን፡ እግዚያብሔር ግን አንቀጹን ያብራራል። መጽሐፋችሁን በኤርሚያስ፡ ምዕራፍ ሁለት እየከፈታችሁ...

23 በጌታ የተወደደ ወንድማችን፡ ወንድም ሊ ቨይል፡ ከእኛ ጋር ስላለ፡ ደስተኛ መሆኔን መናገር እፈልጋለዉ። ይመስለኛል፡ ስሙን ባላስታውሰውም፡ ያ ወንድም እዚህ አለ፡ ወንድም ዊላርድ ክሬስ። ከአርካንሳስ የመጡ ወንድሞችን፡ ወንድም ጆንን እና ሌሎች፡ ከፖፕላር ብሉፍ አካባቢም፡ ወንድም ብሌርን አይቼዋለሁ። እና፡ ኦህ፡ ወንድም ጃክሰን፡ እና ወንድም ራድል፡ እና እኔ—እኔ ልጠቅሳቸው የማልችላቸው... የሁሉንም ሰው ሰም መጥራት ብችል ምኞቴ ነው፡ ነገር ግን ያንን ማድረግ አልችልም፡ ያዉ ትረዱኛላችሁ። ወንድም ቤን ብርያንት፡ እዚህ ጋር ተቀምጦ አይቼዋለዉ፡ እርሱም ሁል ጊዜ የአሜን ጓዴ ነው... ሁሉም ሰው ቤንን በድምፁ ያውቀዋል። ኡህ-ሁህ።

24 አንድ ጊዜ፡ በካሊፎርኒያ ተቀምጠን፡ በሽለቆ ላሉ መልዕክት ሰሰብክ ነበር። እዚያም ትልቅ ድንኳን፡ እና ብዙ አይነት ባላባት ባፕቲስቶች ነበሩ። "አሜን" የሚል ሰው በጭራሽ አልሰማሁም፡ ታውቃላችሁ፡ አንዳንዶች ሴቶች የፊታቸው መዋቢያ እንዳይለቅባቸው ይፈራሉ። **ከዚያ** በኋላ፡ ታውቃላችሁ መጀመሪያ፡ አየር ላይ ሁለት እግሮች፡ እና ሁለት ትልልቅ እጆች፡ ወደላይ እንዲህ ሲዘሉ፡ እና ባለ ጥቁር ጸጉር እየተንቀጠቀጠ፡ "አሜን፡" እያለ እንዲህ ሰጮህ

አየሁ። ወደ ታች ተመለከትኩትና እንዲህ አልኩት፡ “ቤን፡ ከየት መጣህ? ” ከልቡ “አሜን” እያለ ነበር።

25 ሚስቱ በጥቂቱ፡ ስትመለከተው አየሁ። መልካም፡ ጥቁሩ-ፀጉር ትንሽ እየሸሸ ነው፡ ነገር ግን ታውቃላችሁ፡ ያ ችግር የለውም። ያ አያስጨንቃችሁ። እኔም የራሴን፡ ከረጅም ጊዜ በፊት፡ አትቼዋለሁና።

ስለዚህ፡ አሁን፡ መጸለይ አትርሱ።

26 አሁን ወደ ዋናው የአገልግሎቱ ጎን ስንሄድ፡ አስታውሱ፡ ይህን ቃል ካነበብነው፡ እግዚአብሔር ቃሉን ይባርካል። “የታሰበውን ይፈጽማል እንጂ፡ ለእርሱ ባዶ አይመለስም።” እና ቃሉን በማንበብ፡ ሁል ጊዜ ትክክል እንደምሆን፡ አውቃለሁ። ቃሉን ሳነብ፡ እግዚአብሔር ቃሉን ያከብራል።

27 አሁን ለቃሉ ክብር እንቁም። ኤርምያስ፡ 2ኛ ምዕራፍ፡ ከኤርምያስ 2 ላይ፡ 12ኛ እና 13ኛ ቁጥር።

**ኦ... ሰማያት ሆይ፡ በዚህ፡ ተደነቁ፡ እጅግም ደንግጡና፡ ተንጥቀጡ፡ ይላል ጌታ።**

**ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች አድርገዋልና፤ እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል፡ የተቀደዱትንም ጉድጓዶች፡ ውኃውን ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን... ጉድጓዶች፡ ለራሳቸው ቆፍረዋል።**

አሁን አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

28 ጌታ ሆይ፡ ቃልህ ተነቧል። እናም ያንን ቃል እንድታከብረው፡ ባለፉትም ዘመናት እስራኤልን እንደ አብነት ስንመለከት፡ መጽሐፍ ቅዱስም፡ እንደምያስተምረን፡ ቃሉን ባከበሩት ጊዜ ያደረግክላቸውን፡ እና ቃሉን ባላከበሩት ጊዜ ምን እንዳደረክ ማየት እንድንችል፡ ምን ማድረግ እንዳለብንም እንድንማር፡ በዚህ ምሽት ምሳሌውን ወይም ተመሳሳይ ሀሳቡን እንድትሰጠን እንጸልያለን። ስለዚህ፡ በዚህ ቀን ራሳችንን እንዴት መምራት እንዳለብን እናውቅ ዘንድ፡ የምንኖርባትንም ዛሬ ጠዋት እንማር ዘንድ፡ ዛሬ ምሽት በልዩ ሁኔታ እንድትናገረን እንጸልያለን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

መቀመጥ ትችላላችሁ።

29 በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዛሬ ማታ መናገር እፈልጋለሁ፡ ለ—ለአጭር ጊዜ ብቻ፡ **የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች።**

30 እስራኤል ሁለት ታላላቅ ክፋቶችን ሠርቷል፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለ። የሕይወት ምንጭ ከሆነው፡ ከእርሱ አፈነገጡ፡ የሚጠጡትንም ጉድጓድ ለራሳቸው ቈፈሩ። አሁን፡ ይህ አንድ ነገር ነው።

31 ይህን መልዕክት ያሰብኩበት ምክንያት ከምንኖርበት ሰዓት ከምንታገልበት ምክንያት፡ እና ዛሬ ጥዋት ከምናገረው ጋር፡ ተመሳሳይ ስለሚሆን ነው።

32 እስራኤልንም እንደ ምሳሌ እንመለከታለን፡ ማለት፡ እግዚአብሔር ትናንት እንደነበረው ሁሉ፡ ሁልጊዜም ያው ሆኖ መኖር አለበት። እግዚአብሔርም የሚያከብረው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ እርሱም፡ ለሰዎች ያዘጋጀውን መንገዱን ነው። ከዚያ መንገድ በወጡ ጊዜ፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔርን አያስከብረውም።

እግዚአብሔርም ሕዝቡ ምንም ይሁን ምን፡ እንዲያደርጉ ካዘዛቸው ፈቀቅ ሲሉ መከራን ያመጣባችኋል።

ሕግ እንኳ ሰጣቸው፡ "አትንኩ፡ አትያዙ፡ አትቅመሱ።" ክፋታቸው የማድረግ ብቻ ሳይሆን፡ እርሱ አድርግ ያለውን ያለመታዘዝ ክፋት ነው። ስለዚህ ህግም ሁል ጊዜ ቅጣት የሌለው ከሆነ ሕግ ሊባል አይችልም። ምክንያቱም፡ ቅጣት ከሌለው፡ እንግዲያውስ፡ ቅጣት አልባ ሕግ ትርጉም አልባ ነው። ሕግ!

33 አሁን፡ በዚያ ቀን ያደረጉትን፡ እናገኛለን ዛሬ እኛ ከምንሠራው ነገር ጋር፡ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ከሚያደርጉት ነገር ጋር ተመሳሳይ ይመስላል።

34 አሁን እዚህ እንግዳ ነገር እናያለን። "ስለ እነሱም፡ ለራሳችሁ፡ የተቀደዱ፡ ጉድጓዶችን ቆፈራችሁ፡" ሲላቸው፡ ለአንዳንዶች እንግዳ ሊሆንባቸው ይችላል። አሁን፡ ምናልባት አንዳንዶቻችሁ የውኃ ጉድጓድ ምን እንደሆነ አታውቁም። ጉድጓድ ምን እንደሆነ የሚያውቅ ስንት ነው? መልካም፡ ሁላችሁም። በእርሻ ቦታ ያደጋችሁ ከሆነ፡ የውሃ ጉድጓድ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። የ—የውኃ ጉድጓድ—ምን እንደነበር ለማወቅ፡ ከአንዱ በቂ ነፍሳትን እንደጠጣሁ አስታውሳለሁ።

የቅጠል ዳስ ባለበት፡ ሃገር ሰሰበክ፡ ታውቃላችሁ፡ ከ—ከዝናብ ውኃ የወረደ፡ እንሰራ የሞላ የጉድጓድ ውሃ በዚያ ተቀምጦ፡ እና ትንሽ የቆየ ነገር ነው። እና—በማታ ጊዜ፡ ነፍሳት፡ ወደ ውስጥ ይገባሉ። ስለዚህ የጉድጓድ ውሃ ምን እንደሆነ አውቃለው።

35 ጉ—ጉድጓድ ማለት፡ የምንጭ ውሃን ለመተካት፡ መሬት ውስጥ ተቆፍሮ የ—የሚዘጋጅ ቦታ ነው። ሰዎች የውኃ ምንጭ ከሌላቸው፡ የ—የውኃ ጉድጓድ ያበጃሉ። በሌላ አገላለጽ፡ ጉድጓድ ማለት ሰው-ሰራሽ የውሃ ጋን፡ ወይም ሰው-ሰራሽ መሬት ውስጥ የሚገኝ ምንጭ፡ ሰው ውሃ ለመያዝ እና፡ ለመጠቀም የ—የቆፈረው፡ ጉድጓድ ማለት ነው። ምናልባትም፡ በተለያየ መንገድ ይጠቀሙታል፡ አንዳንዶቹ ለማጠብ ይጠቀሙታል፡ አንዳንዶቹም ለመጠጥ ይጠቀሙታል። የሆነ ጊዜ የምንጠቀመው፡ ውኃችን በሙሉ፡ ከጉድጓድ ነበር። ውኃውን ወደ ላይ ለማውጣት፡ የሆነ ጠምጥማችሁ ማዞር፡ ማዞር፡ ማዞር፡ ማዞር፡ ያለባችሁ አሮጌ ነገር ነበረው፡ በላዩ ላይ ውኃውን ከጉድጓድ ውስጥ ለማውጣት፡ ትንሽ ባልዲዎች ነበሩት።

36 ስለዚህ፡ የውኃ ጉድጓድ ከምንጭ የምለይበትን አንድ ነገር እናስተውላለን። አሁን፡ የውሃ ጉድጓድ ባዶ ሊሆን ይችላል። የ—የ—የውሃ ጉድጓድ ራሱን በውሃ መሙላት አይችልም። አስተማማኝ... አ—አይደለም። በውሃ ጉድጓድ ላይ መታመን አትችሉም። በበጋ ወይም በክረምት ከሚዘንበው ዝናብ ላይ የሚተማመን እና ጥገኛ ነው፡ ምንም ይሁን ምን... ብዙውን ጊዜ፡ በክረምት ወቅት በረዶ እና ዝናብ ሲመጣ፡ ከዚያም ውሃው ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ይገባል። እናም ያንን ውሃ ካላገኙ፡ ከዚያም እናንተ—እናንተ ምንም ውሃ አይኖራችሁም። ሁሉም—ሁሉም... ይደርቃል። ራሱንም መሙላት አይችልም። አሮጌው የውሃ ጉድጓድ ራሱን መሙላት አይችልም። መሙላቱን የሚያገኘው ከ—ከሚዘንበው ዝናብ ነው።

37 እናም ስለ ውሃ ጉድጓድ ሌላም ነገር እንድታስተውሉ እፈልጋለው። አብዛኛውን ጊዜ፡ የሚታገኙት፡ ወይም በእኛ ቦታ የነበረበት መንገድ፡ የውሃ ጉድጓድ... ብዙውን ጊዜ ጎተራው የቤቱን እጥፍ ያህላል፡ እና አብዛኛውን ጊዜ፡ ውሃውን ከጋጣው ወደ ጉድጓዱ ያፈሳሉ። ያንን እርጌ ጉድጓድ በደንብ አስታውሳለሁ፡ የፍሳሽ ማስወገጃ... ቱቦዎች—ከጋጣው ውስጥ ሲያስተላልፉት፡ ሲያስገቡበት፡ ያ ጉድጓድ ከጋጣው በመጣ ውሃ ይሞላል፡

ስለዚህ ውሃው፡ በደረቅ ጊዜ እንስሳት በረጋው ጓሮ ውስጥ ሲረጋግጡት ከነበረው፡ ከጋጣው ጣሪያ ላይ ተጠራርጎ ሲወርድበት፡ የጎተራው የጓሮው ቆሻሻዎች በሙሉ፡ በጋጣው ላይ ይከማቻሉ። ከዚያም ውሃው መጥቶ ሁሉንም ከጣሪያው ላይ አጥቦ፡ ሰው-ሰራሽ በሆነው ገንዳ ይጨምረዋል፡ ከዚያም በሰው-ሰራሽ ቧምቧ ያልፍና፡ ሰው-ሰራሽ በሆነ ጉድጓድ ውስጥ ይጨምራል። ጉድጓድ ስትቆፍሩ፡ የተበላሸ ነገር ካላገኛችሁ፡ ምን ልታገኙ እንደምትችሉ አላውቅም። አዎን፡ ወዳጄ! ሁሉም ሰው-ሰራሽ ነው፡ መሆን በቻለው አቅም ሁሉ ቆሻሻ ነው።

38 ታውቃላችሁ፡ እንዲህ እንለው ነበር... የማጣሪያ ጨርቅ እናደርግበታለን። ያ ምን እንደነበር ታውቃላችሁ? ሁሉንም ነፍሳትን፡ እና ከጎተራው ከላይ እና—ከዙርያ ሁሉ የሚመጡ ነገሮች፡ ፈሰው ወደ ጉድጓግ እንዳይገቡ፡ ለመያዝ በላዩ ላይ የማጣሪያ ጨርቅ፡ ይደረግበታል፡ ቆሻሻው ሁሉና ለሎች ነገሮችን የምንችለውን ያህል ለ—ለመያዝ፡ በላዩ ላይ የ—የማጣሪያ ጨርቅ እናደርግ ነበር። እርግጥ ነው፡ በትክክል ቆሻሻ የሚባለውን ነገር አይይዝም፡ ወደሱ ሊወርዱ የሚወድቁ ትላልቅ ተወርዋሪዎቹን ይይዛቸዋል። ነፍሳት ሊወድቁበት ይችላሉ፡ ወደ ውስጥ ዘልቆ የሚፈሰው ግን የነፍሳት ጭማቂ ውኃው ነው። ስለዚህ፡ የነተበ ጉድጓድ ሲኖራችሁ—በእውነቱ ትርምስምስ ያለ ነገር ይኖራችኋል።

39 በዚያ ውስጥ፡ ውኃውን ጥቂት ቀናት ስታቆዩት፡ የተመረዘ ውኃ ይሆናል። ውኃውን በጉድጓድ ውስጥ ስታቆዩት፡ የተመረዘ ውሃ ይሆናል። እና እ—እንቁራሪቶች፡ እንሽላሊቶች፡ እና እባቦች፡ የተሞላ ይሆናል። "ዊግል-ቴይልስ" ብለን እንጠራቸው ነበር፡ ትንንሽ ነገሮች... ጥገኛ ነፍሳት ይሁኑ... አይሁኑ አላውቅም፡ ብቻ... እንጃ፡ ምን ብላችሁ እንደምትጠሯቸው አላውቅም። ብቻ ትንንሽ ነገሮች ወደ ውኃው ውስጥ ይገቡበታል፡ ባለ ዊግል-ቴይልስ ብለን—እንጠራቸዋለን። ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። ስለ ምን እንደማወራ የምታውቁት ስንቶቻችሁ ናችሁ? ኦህ፡ ታዲያስ፡ በእርግጠኝነት፡ ያገር ተወላጆች ሁላችሁ ታውቃላችሁ። ሙሉ በ ሙሉ ውኃው ይተኛል፡ መተኛቱን የሚወዱ ነገሮች አብረው ይመጣሉ። በእርግጥ ይመጣሉ፡ ምክንያቱም ውኃው የተኛ ስለሆነ። ምክንያቱም ውኃው የተኛ ስለሆነ፡ የተኛ ውኃ የሚወዱ እንስሳትን ወደዚያ ይስባል።

40 ያ ሁሉ ዛሬ ያሉ አብያተ ክርስቲያኖቻችን ምሳሌ ነው። ጥለን የሄድን ይመስለኛል... ልክ እንደ እስራኤል፡ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ከሠራቻቸው ከታላላቅ ኃጢአቶች አንዱ፡ እርሱን፡ የሕይወት ውኃ ምንጭ ትታ፡ ለራሳቸው ሰው-ሰራሽ የውሃ ጉድጓድ መቆፈራቸው ነው። እንደዛ አይነት ውኃ ለሚወዱ ነገሮች ሁሉ መኖርያ ሆነች። እንሽላሊቶች፡ እንቁራሪቶች፡ እና ሁሉም አይነት ንፁህ ያልሆኑ ጀርሞች፡ በውስጧ ይኖራሉ፡ ምክንያቱም ሰው-ሰራሽ የውኃ ማጠራቀሚያ

ስለሆነች። በዚህ በውኃ ማጠራቀሚያም እነዚህ ነገሮች ይቆያሉ፡ ይህም የዘመናችንን ሃይማኖት ተቋሞች ትክክለኛ ምሳሌ ነው።

41 "አሁን፡" እንዲህ ትላላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ለምን እነዚያን ሰዎች በጣም ትመታቸዋለህ? "

መመታት አለበት። ሊመታ ይገባዋልና። በስተመጨረሻው የአውሬውን ምልክት የፈጥራልና፡ አምልጡ። አስታውሱ፡ ያ እውነት ነው! የአውሬው ምልክት ይሆናል። የሃይማኖት ተቋም በትክክል ወደዛ ይመራል። በኃይል፡ ለማስገደድ፡ አሁን በመንገዱ ላይ ነው።

42 የበፊቱን የሮማን ግዛት ተመልከቱ። ወደዚያ ወደ ሃይማኖት ክህደት ምልክት የመራቸው ያ ነው። ማንም ሰው ከአውሬው ምልክት ውጭ ሊገዛ ወይም ልሸጥ እንደማይችል ታውቃላችሁ። ምልክቱ ሊኖረው ይገባል።

43 በምድር ላይ ሁለት የሰዎች መደብ ይኖራል፡ የእግዚአብሔር ማኅተም ያለባቸው፡ እና የአውሬው ምልክት ያላቸው። ሁለት መደብ ብቻ፡ ስለዚህ እናንተም አንደኛው ወይም ሌላኛው ሊኖራችሁ ግድ ነው። ክህደት ይመጣል፡ የ—የሃይማኖት ም—ምልክት፡ ሃይማኖትን መካድ ይሆናል።

44 ለአውሬውም ምስል ይኖረዋል። እንደተማርነውም፡ ሮም፡ አውሬ እንደነበረች፡ አሁንም የአው-... እንደሆነች፡ እና ሁሌም እንደምትሆን፡ እናውቃለን። በትክክል። ሌላ ነገር ለማግኘት ምንም መንገድ የለም። ሮም!

45 እና ሮም ምን አደረገች? ከአረማዊ ሮም ወደ ጳጳስ ሮም ተለወጠች፡ እናም ሥርዓቷን አደራጀች፡ ሰውን ሁሉ ወደ አንዲት ሃይማኖት እንዲገባ፡ እምቢ ካለ እንዲገደል የሚያስገድድ አለማቀፋዊ ሥርዓት ዘረጋች።

46 ዩናይትድ ስቴትስ በዚህ ነገር ላይ መታየቷ እንግዳ ነገር ነው፡ እና እንደ በግ ጠቦት ይመስላል። ሁለት ትናንሽ ቀንዶች እንዳሉት በግ፡ የሲቪል እና የቤተ ክርስቲያን መብቶች። ከጥቂት ጊዜ በኋላም፡ ያ በግ የነበረ ነገር፡ እንደ ዘንዶ ሲናገር እና ከሱ በፊት የነበረው ዘንዶ ሲሰራበት በነበረው ስልጣን ሲከውን እናየዋለን። መጽሃፍ ቅዱስም "ለአውሬው ምስል እንሥራለት፡" ብለው እንደተናገሩ ይመሰክራል። አንድን ነገር የሚመስል የሆነ ምስል ነው። እናም ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖቷን፡ በከዳችበት ሁኔታዋ፡ ለሮም ስልጣን ምስል የሆነውን፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስልን፡ እያቋቋመች መሆኗን አሁን እናያለን፣ አረማዊቷ ሮም... ወይም ጳጳሳዊት ሮም ያደረገችውን ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ህዝቡን ያስገድዳሉ። ስለዚህ፡ ሌላ መንገድ የለም፡ ሌላ ነገር የለም። እውነታው ግን ያ ነው።

47 በእድሜዬ፡ በዘመኔ ሁሉ፡ የምመታቸው ምክንያቱ ይህ ነው፡ መመታት ስላለባቸው ነው። ጥሪው፡ ሲመጣ፡ "ሕዝቤ ሆይ፡ ከኃጢአትዋ እንዳትተባበሩ፡ ከእርስዋ ዘንድ ውጡ!"

48 እንግዲህ፡ እኔም ያ ነገራቸው ከቆሸሸ፡ ከበከተ ጉድጓድ ጋር አመሳስለዋለሁ። "እርሱ የሕይወት ምንጭ ነውና። የሕይወት ውሃ ነውና።" ሰውም ያንን ትቶ፡ ቆሻሻን ብቻ የሚይዝ ጉድጓዶችን ለራሱ ይቆፍራል። መያዝ የሚችለው ያን ብቻ ነው። የሃይማኖት ተቋም የሚያደርገው ያንኑን ነው፡ የሚመጣውን እና መቀላቀል የሚፈልገውን ሁሉን ይይዛል። የተወሰነ

ገንዘብ ካገኙበት፡ ወይም በሆነ መንገድ ከለበሱ፡ ዘልቆ እንዲገባ እንዲሁ ይፈቅዱለታል። ማንም ቢሆን፡ ከየትም ቢመጣ፡ ምንም ይሁን ምን፡ በማንኛዉም መንገድ እንዲሁ ይፈቅዱላቸዋል።

49 አሁን በድጋሚ፡ ስንመለከተው፡ ማለት፡ ይህ የተሰራ የአውሬውን ምልክት... አሜሪካ ቁጥር አስራ ሶስት እንደሆነች እናያለን። ከአሥራ ሦስት የቅኝ ግዛቶች ተወለደች። አሥራ ሦስት ኮከቦች፡ እና አሥራ ሦስት መሰመር ያለው ባንዲራ አላት። በራእይ መጽሐፍ በምዕራፍ 13 ላይ ትታያለች። በሳንቲሞቻችን ላይ እንዳለው ምሳሌ፡ አሜሪካ ሁሌም ሴት ናት። በሳንቲም ውስጥ ያለው፡ የኢንዲያን ራስ ሳይቀር፡ የሴት ፕሮፋይል ነው። እናውቀዋለን፡ ታርኩን እናውቃለን። ነገሩ ሁሉ፡ የነጻነቱ ደወል፡ እና ሌላው ነገር፡ የነጻነት... የነጻነት ሃውልት፡ ሁሉም ነገር፡ ሴታዊ ነው። ባለ አስራ ሶስት ቁጥር፡ ሴት። አያችሁ? አሁን፡ እነዚያን—ነገሮች ማየት በጣም ቆንጆ ነው።

50 አሁንም ከመጨረሻው ጊዜ በፊት፡ ሰባት ነገሮች እንደሚሆኑ፡ በእግዚአብሔር መገለጥ ወይም በራዕይ በ1933 ተንብያለሁ። ያም፡ አንደኛውም፡ ያ፡ "በዚያን ጊዜ አምባገነን እየሆነ የነበረው፡ ሙሶሎኒ፡ አምባገነን እንደሚሆን፤ ደግሞም፡ ወረራ አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ ወርዶ ኢትዮጵያንም እንደሚይዛት፤ መንፈሰም፡ 'በእግሩ ስር ይወድቃሉ፡'" ብሏል።

51 ከብዙ-አመታት በፊት እዚህ በሬድማን አዳራሽ ያንን እያልኩ የሚያስታውሱኝ፡ በዚህ ተበርናክል ውስጥ ከነበሩት፡ ቀደምት መካከል፡ አሁንም የቀሩት ይኖራሉ ብዬ አሰባለው። ያኔ በሩዝቬልት የመጀመሪያ የስልጣን ዘመን ላይ፡ በሬድማን አዳራሽ በሰበኩ ጊዜ የነበሩት ሰዎች፡ ዛሬ ማታ፡ ያኔ N.R.A. ባካሄዱበት ወቅት፡ ከነበሩ መካከል ህንጻ ውስጥ አንድ ሰው ይኖር ይሆን? እዚህ ውስጥ አንድም እንደማይኖር እገምታለሁ። አንድ አለን? አዎ፡ አዎ፡ አንድ፡ አንድ አለ። አዎ፡ ወይዘሮ ዊልሰን አለች፡ አስታውሳታለሁ። ከኋላ የተቀመጠችው፡ ባለቤቴም ጭምር። በዚያ ቀን ከነበሩት፡ ከበፊቱ ትውልድ ሁለት ብቻ ቀርተዋል።

ማለት፡ ይህ N.R.A. የአውሬው ምልክት ነው ይሉት ነበር፡ እኔም እንዲህ አልኩ፡ "በፍጹም አይገናኝም፡ አይደለም። የአውሬው ምልክት ከሮም ይመጣል። እንጂ ከዚህ አይመጣም። ስለዚህ ይህ የአውሬው ምልክት ሊሆን አይችልም።"

52 አሁንም እነዚህ ነገሮች እንደተባሉ አስታውሱ። እንዲህ ብያለሁ፡ "አዶልፍ ሂትለር ወደ ሚስጥራዊ ፍጻሜው ይመጣል። በአሜሪካ ላይም ጦርነት ያውጃል። ታላቅ—አንድ—ታላቅ ግንብ ነገር ይገነባሉ፡ በእርሱ ውስጥ እንኳ ይኖራሉ። በዚያም፡ አሜሪካውያን በዚያ ላይ አስቃቂ ድብደባ ያደርሳሉ።" መገንባት ከመጀመሩ ከአስራ አንድ አመት በፊት፡ የሲግፊሪድ ላይን ይባል ነበር። ከዚያም እንዲህ አልኩ፡ "ነገር ግን ወደ ፍጻሜው ይመጣል፡ ሰቴቶቹ ጦርነቱን ያሸንፋሉ።"

53 ከዚያም፡ "እነሆ ሶስት ኢዝሞች፡ ናዚዝም፡ ፋሺዝም፡ እና ኮሚኒዝም፡" ይመጣሉ አልኩ። "እነዚህም በሙሉ በኮምዩኒዝም ይዋጣሉ። ሩሲያ፡ ሁሉንም በኮሚኒዝም ትውጣቸዋለች፡" ብዬ ተናግሬ ነበር።

54 እንዲህም ብያለው፡ “ከዚያ በኋላ ሳይንስ እጅግ ያድጋል፡ የሰው ልጅ እውቀትም ይበዛል፡ እንቁላል የሚመስል አውቶሞቢል እስኪሰራ ድረስ ብዙ ነገሮችን እስኪፈጥር ድረስ፡ በጣራቸው ላይ መስታወት መሳይ ነገሮች ያሏቸው፡ በመሪ ሳይሆን በሌላ ኃይል የሚዘወሩ እስከመሰራት ድረስ ብልህ ይሆናሉ።” መኪናው አሁን ደርሰውበታል።

55 ከዚያም እንዲህ አልኩ፡ “ያኔ የሴቶቻችን ሞራል ለአሕዛብ ሁሉ ውርደት እስኪሆኑ ድረስ፡ ዝቅ ባለ ነገር ላይ ይወድቃል። የወንድን ልብስ ይለብሳሉ። ውስጠኛው ልብስ ቀርቶ እንዲሁ ልብሳቸውን አውልቀው እስኪቀሩ ድረስ እንዲሁ ይሆናል፡ ይኸው ነው። በስተ መጨረሻም፡ የበለስ ቅጠል፡ ወደ መልበስ ይደርሳሉ።”

ካስተዋላችሁ፡ ባለፈው ወር **ላይፍ** መጽሔት ላይ፡ የበለስ ቅጠሎችን ያገለደመች ሴት ለቀው ነበር። ያም ደግሞ የማታ ልብስ፡ ወይም ጋዋን፡ ማታ ላይ የሚለብሱት አይነት ነገር ነው፤ አልፎ የሚያሳይ፡ ስስ ነገር፡ የተወሰነ የሰውነት ክፍሏን ቅጠሎቹ ሸፍነውታል፡ ከላይ በኩል፡ ገላ የሚያሳይ፡ ማሰሪያ አልባ፡ ወይም ማሰሪያ የሌለው፡ የመታጠቢያ ልብስ ነበር። እነሆም እነዚህም ነገሮች እንዴት ተፈጸሙ!

56 በመቀጠል እንዲህ አልኩ፡ “በሜሪካ ውስጥ፡ አንዲት ሴት እንደ ታላቅ ንግስት ወይም እንደ ሌላ ነገር ስትቆም አየሁ። እሷም ስትታይ ቆንጆ ነበረች፡ በልቧ ግን ክፉ ነበረች። አገሪቷን ረግጣ፡ ከእግሯ ስር እንድትሄድ ታደርጋለች።”

57 ከዚያም አልኩ፡ “በመጨረሻ፡ ወደ ምስራቅ ዞሬ እንድመለከት ነገረኝ። እኔም፡ ስመለከት፡ ዓለም የፈነዳች፡ ስትመስል፡ አየሁ። እኔ ማየት የቻልኩትን ያህል ርቀት አየሁ፡ ከምድር ውስጥ ተሰባብረው ከወጡ—አለቶች፡ እና ጉቶዎች በቀር የቀረ ነገር አልነበረም።”

እነዚህም የዓለም ፍጻሜ ከመሆኑ በፊት የሚፈጸሙ ነገሮች ናቸው። ከሰባቱም አምስቱ በሠላሳ ሦስት ዓመታት ውስጥ ተፈጽመዋል። ወደ መጨረሻው ዘመን ተመልሰን፡ እዚያው ነን እኛ!

58 ያን ጊዜ የሃይማኖት ተቋምን ተቃውሜ ተናገርኩ። ዛሬ ማታም፡ ቆሻሻ ወደ ውስጥ የሚጣልበት፡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ እንደሆነ፡ እስከ አሁን ድረስ አምናለሁ። እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ነገር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ይቀበላል ብዬ አላምንም፡ ምክንያቱም የእርሱ ከመባሉ በፊት ከእግዚአብሔር መንፈስ ዘንድ መወለድ እና ከዚያም መንጻት አለበት። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ወደ ምስጢራዊው ወደ ክርስቶስ አካል ተጠምቀናልና።

59 አዎን፡ ይህ የውሃ ጉድጓድ ስርአት ለሃይማኖት ተቋም ፍጹም ምሳሌው ነው። እግዚአብሔር እንደሚቃወመውና፡ ከእሱ ጋር እንዳልሠራ በዘመናት ሁሉ አስመስክሯልና፡ ጠቢብ ሰው ፈጽሞ እንዳይገባበት ሊመለከተው ይገባል። ማንኛውም ቡድን... አንድ ሰው በማንኛውም ጊዜ፡ እንደ ሉተር፡ ዌስሊ፡ እና ስሚዝ፡ እና ካልቪን፡ እና እንደመሳሰሉት፡ መልእክት ይዘው ተነስተው፡ መደራጀት በጀምሩ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ነገሩን በመደርደሪያው ላይ ያስቀምተዋል እንደገናም በሪቫይቫል ፈጽሞ አይጎበኘውም።

60 ተመልከቱ በታሪክ ውስጥ። እግዚአብሔር አንድን የሃይማኖት ተቋም ወስዶ፡ ከውስጡ መነቃቃትን ያደረገበት ጊዜም፡ ቦታም ፈጽሞ የለም። ከዚያም፡

ያ በእግዚአብሔር ፊት ቆሻሻ ነገር እንደሆነ፡ ታሪክ እና መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል፡ ስለዚህ ከእሱ ጋር ምንም ማድረግ አልፈልግም። የምቃወመው ለዚህ ነው። ህዝቡን ከእሱ ውስጥ ለማውጣት እየሞከርኩ ነው።

61 ልክ እንደ እስራኤላውያን ሁሉ፡ አሁን ደግሞ እስራኤልን፡ ለአብነት እንድንመለከት፡ ተጋብዘናል። እነርሱ፡ ከዚያ ምንጭ ጋር እስከቆዩ ድረስ፡ ሁሌም ደህና ነበሩ። ነገር ግን ሰው-ሰራሽ ጉድጓድ፡ ለራሳቸው መቆፈር በጀመሩ ጊዜ፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔር በሜዳ ተዋቸው። እሱ ለእኛም እንዲሁ ያደርጋል። "የሕይወት ውኃ ምንጭ የሆነውን፡ እርሱን ትተውታል።" እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ያቀረበው ቅሬታ ያ ነበር። "ሊሉት የሚችሉትን ነገር ለመፍጠር፡ 'ያደረግነውን ታያላችሁን!'"

62 አሁን፡ በ—በሙሴ ጉዞ ጊዜ፡ እግዜአብሔር በጸጋው ነብይ በሰጣቸው ጊዜ፡ በፊታቸውም ይሄድ ዘንድ የእሳት ዓምድ ሰጥቷቸው፡ በምልክትና በድንቅ አጸድቆት ነበር፡ ጸጋው እነዚህን ሁሉ ነገር አቀረበ፡ እስራኤል ግን አሁንም ሕግ ትፈልጋለች። ሕግን ለመቀበል፡ ጸጋን እምቢ አሉ።

ዛሬ ህዝቡ የሚያደርገው ይህንኑን ነው። የሃይማኖት ተቋምን ስርአት ለመቀበል፡ ቃሉን እምቢ ይላሉ፡ ምክንያቱም በዚያ ማድረግ የፈለጉትን ነገር ማድረግ እና መቀበል ይችላሉና። ነገር ግን በክርስቶስ ማድረግ አትችሉም! በክርስቶስ ለመሆን ንፁህ እና ግልፅ፡ ሆናችሁ መምጣት አለባችሁ።

63 ለሰው-ሰራሽ ስርአት ወይም ለጉድጓድ ብሎ፡ የምንጭ ውሃ ጉድጓድን መተው፡ የሆነ ሰው ያንን ሲያደርግ ማሰቡ አይከብዳችሁም ወይ? እንዲሁ አይነት ሰው የአእምሮ ሁኔታው እስኪ አስቡት ከምንጭ ውኃ ሲጠጣ የኖረ ሰው፡ እንቁራሪቶች፡ እንሽላሊቶች፡ እና ዊግል-ቴይሎች፡ እና ልዩ ልዩ ነገር ላሉበት ሰው-ሰራሽ ጉድጓድ ይተዋልን?

ትክክል ስለ መሆኑ ምክንያታዊ እንኳ አይመስልም፡ ህዝቡ ያደረገው ግን ይህንኑ ነው። የእግዚአብሔር ምንጭና የኃይሉ ምንጭ፡ የሆነውን ቃሉን ትተው፡ ከጉድጓዶች ለመጠጣት፡ ለራሳቸውም ጉድጓዶች አደረጉ። ያኔ እንዳደረጉት ሁሉ፡ አሁን አድርገውታል። እንዲህ ይላሉ...

እንዲህ አለ፡ "እኔን ትተውኛል።" እዚህ ጋር እንዲህ ብሏል፡ በኤርምያስ 2:14 ላይ፡ ወይም 13፡ ላይ። እንዲህ ብሏል፡ "እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ፡ ትተውኛል።"

64 አሁን፡ የውሃ ጉድጓድ ምን እንደሆነ አይተናል። ምን እንደምይዝ አየን። እንዴት እንደተሰራ አይተናል። ከቆሸሸ ጣሪያ ላይ የሚወርድ ሰው-ሠራሽ ነገር ነው። የሚዘንበው ውሃ፡ በቆሻሻ ጣሪያ ላይ ይወድቅና፡ ቆሻሻውን ብቻ አጥቦ፡ በሰው-ሰራሽ ገንዳ አርጎ፡ በሰው-ሰራሽ ቱቦ በኩል፡ ወደ ሰው-ሰራሽ ታንከር ውስጥ ያስገባዋል። እና ሁሉም ቆሻሻዎች፡ እና—ጀርሞች፡ እንሽላሊቶች፡ እንቁራሪቶች፡ እና እንደዛ አይነት በምድር ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ፡ እዛ ውስጥ ይሰበሰባሉ። እና፡ አስተውሉ፡ እነዚህ ሁሉ እርኩስ እንስሳት ናቸው፡ ዊግል-ቴይሎች፡ በተኛ ውሃ ውስጥ ይኖራሉ። ዊግል-ቴይል በንጹህ ውሃ ውስጥ መኖር አይችልም። በንጹህ ውሃ ውስጥ ከኖረ፡ ይሞታል። መኖር የሚችለው በተኛ ውሃ ውስጥ ነው።

65 ለዚያም ነው ዛሬ ከብዙ ጥገኛ ነፍሳት ጋር የሚኖረው። በመንፈስ ቅዱስ ንጹህ ውኃ ውስጥ መኖር አልቻላችሁም። ለዚህም ነው ቃሉን አጥብቀው የሚቃወሙት፡ እናም እንዲህም ይላሉ “ራሱን፡ ይቃረናል። ተራ ነገር ነው” ይላሉ። ምክንያቱም በውስጡ የሚርመሰመሱበት የተኛ ውኃ ያለበት ገንዳ ስላላቸው ነው። በትክክል።

ልክ ከእንቁራሪቶች፡ እና ከእንሽላሊቶች፡ እና ከእንቁሪዎች እና ከመሳሰሉት ጋር ተመሳሳይ ነው። ለመኖር፡ የረጋ ውኃ ወይም የተኛ ውሃ ያስፈልጋቸዋል፡ እዛ ለመኖር ተፈጥሯቸው ነው። ተፈጥሮውን እስካልቀየራችሁት በቀር እንስሳውን መቀየር አትችሉም።

ለሰውም ተፈጥሮውን እስካልቀየራችሁ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲመለከት ማድረግ አትችሉም፡ ተፈጥሮው ከማንነቱ፡ ወደ እግዚአብሔር ልጅነት በተቀየረ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ እርሱ ይመጣል። የእግዚአብሔርን ቃል የጻፈ መንፈስ ቅዱስ ነው!

66 ዛሬ እዚህ ካለው፡ ከሚገኘው ጓደኛዬ ከዶክተር ሊ ቫይል ጋር፡ እየተነጋገርኩ ነበር። እና በጣም የስነ-መለኮት ምሁር ነው፡ ስለዚህም ብዙ ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ አንዳንድ ጥሩ ውይይቶችን እናደርጋለን። በጣም ብልህ ነው።

እና ስለ መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ማስረጃ ምን እንደሆነ ታስባለህ ብሎ አንድ ጊዜ ጠየቀኝ፡ “በልሳኖች መናገር ነውን? ” ከብዙ አመታት በፊትም ነበር።

እንዲህ አልኩት፡ “አይ፡ እንደዛ አላይም።”

እንዲህ አለኝ፡ “እኔም የተማርኩት እንደዚያ ቢሆንም።” “እኔም እንደዚያ አላየውም፡” አለኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ማስረጃው ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ”

67 እንዲህ አልኩት፡ “እኔ የማስበው፡ ትክክለኛ ማስረጃ ፍቅር ነው።” ስለዚህም ጉዳይ መነጋገር ጀመርን።

እንግዲህ እኔም “ሰው ፍቅር ከሆነ፡” የሚል ነገር ልዩ ነገር አድርጌ ስላሰብኩት እሳቡን ይዤ ቆየሁ።

አንድ ቀን ግን፡ ጌታ፡ በራእይ አቃናኝ። እርሱም፡ “የመንፈስ ቅዱስ ማስረጃ ቃሉን መቀበል ለሚችሉ ነው፡” አለኝ፡ ፍቅርም አይደለም፡ በልሳኖች መናገርም አይደለም፡ ነገር ግን ቃሉን መቀበል ነው።

68 ከዚያም ዶክተር ቨይል፡ “መጽሓፍ ቅዱሳዊው ይኸው ነው፡” አለኝ፡ እንዲህ አለ፡ “ምክንያቱም፡ በዮሓንስ ወንገል 14፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ ‘መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ እኔ ያስተማርኳችሁን እነዚህን ነገሮች፡ ይገልጥላችኋል፡ የሚመጣውንም ያሳያችኋል።’”

ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ማስረጃ ይህ ነው! እስካሁን ምንም ስህተት ነግሮኝ አያውቅም። ማለት፡ “የመንፈስ ቅዱስ ማስረጃ፡ ቃሉን ማመን መቻሉ ነው።” መቀበል ትችላላችሁ።

ምክንያቱም ኢየሱስ፡ “መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ፡ በልሳኖች ትናገራላችሁ፡” በፍጹም አላለም። መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ፡ ከእነዚህ ነገሮች አንዱንም ታደርጋላችሁ፡ ብሎ አያውቅም። ያለው ግን፡ “እነዚህን የእኔን

ነገሮች ወስዶ ያሳያችኋል፡ የሚመጣውንም ያሳያችኋል።” ስለዚህ ኢየሱስ ራሱ እንዳለው፡ የመንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ማስረጃ ይኸው ነው።

69 ስለዚህ ይህ ሁሉ ስሜት እና ሰዎች ያላቸው እስካሁንም የሚኖሩበት ነገር፡ ለምን እንደሚያደርጉት ማየት ትችላላችሁ። አያችሁ፡ የሃይማኖት ተቋም፡ ወይም የተኛ ውኃ ገንዳ ይሆናል፡ ፍጹም በ-… በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚሰራ የሃይማኖት ተቋም በጭራሽ አይኖርም። መሆን አይችልም፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ልትሾሙትም ወይም ልታደራጁትም አትችሉም። አትችሉም፡ ዋዳጄ!

70 ነገሩ ይህ ነው፡ ቃሉን የሚያምን ብዙ ሰው ታገኛላችሁ፡ ቀጥላችሁ መደራጀትን እንዲጀምሩ ታደርጋላችሁ። መጀመሪያ የሚሆነው ነገር፡ ምንም ልትሏቸው የማትችሏቸው ቅንጡዎች ይበዙበታል። እነርሱ ስለሚቆጣጠሩት፡ ምንም ማድረግ አትችሉም። የእግዜብሔር ስርአት አይደለም። አይደለም፡ ከዚያ የወጣ እንደሆነ እናውቃለን። እያንዳንዱ ሰው **በዚህ፡ በዚያ፡** እና **በሌላው** የሚያመቻምቹበት፡ የውኃ ጉድጓድ መሆን ይጀምራል፡ አባላትን ወደዚያ ለማስገባት፡ ወይም ሰዎች እንዲገቡ ለማድረግ ብቻ ነው።

71 ይህ ሥርዓት የጀመረው፡ እስራኤላውያን በኖሩበት ዘመን፡ እነዚህን የውኃ ጉድጓዶች ሲቆፍሩ እንደሆነ፡ ተረድተናል። ጉድጓዶችንም የቆፈረ አንድ ሰውና የፈሪሳውያን ማሕበር ሰዎች ነበሩ። ሄሮድስም የሚባል ሰው ነበራቸው፡ እርሱም አዋጅ ነጋሪና፡ የመንግሥት ገዢ ነበረ።

እናም በሃይማኖት ተቋም ያልተዋኘውን ሰው ለመስማት ወደ እርሱ ወረደ። እርሱም ነብይ ነበር። ነብይ ሆኖ የሃይማኖት ተቋም የሚጠላ እንጂ፡ ግንኙነት ኖሮት የሚያውቅ መቼም አልነበረም። ይህ ነብይ እንዲህ ማለት ጀመረ፡ “በልባችሁም፡ ‘አብርሃም አባት አለን፡’ ማለትን አትጀምሩ፡ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሳለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና።”

72 እነርሱም እርሱን እንዲሰማ ባለስልጣን አመጡ። ይህም ባለስልጣን የወንድሙን ሚስት ወሰዶ፡ አገባት። ይህ ሰው ወደ ፊቱ መጥቶ ምን አለው? እንዲህ የሚላቸው፡ እና የሚያመቻምች መሰላቸው፡ “አሁን፡ ጌታዬ፡ እነሆ፡ ለእርሶ ወንበር **እዚህ** ተዘጋጅቶሎታል። ለእርሶም የሚመጥን… ዛሬ እኔን ለመስማት በመምጣትዎ በጣም ደስ ብሎኛል።”

ዮሐንስ ግን ፊት ለፊቱ ሄደና፡ “እሷን መውሰድ ለአንተ አልተፈቀደም፡” አለው። መጀመሪያ እንዲህ አለው፡ ስለ ሃጥያቱ በታላቅ ድምጽ ነገረው።

73 አያችሁ፡ የሃይማኖት ተቋሞች አንድ ወንድ ከሴቶች ጋር የሚኖርበትን የተኛ ውኃ ገንዳ ይሰራሉ፡ ሴቶችም ጸጉራቸውን ይቆረጣሉ፡ አጭር ይለብሰሉ፡ ሌሎች ነገሮችንም ያደርጉና፡ ራሳቸውን፡ ክርስቲያን ነን ብለው ይጠራሉ።

ከእግዚአብሔር የሆነው፡ እውነተኛው ምንጭ ግን፡ ሃሌ ሉያ፡ ገፍትሮ ስለሚያስወጣው፡ በውስጥ መቀመጥ አይችልም። “የሕይወት ውኃ ምንጭ እኔ ነኝ። ለራሳቸው ሌላ ጉድጓድ ለመቆፈር፡ እኔን ትተውኛል።”

74 አሁን፡ የሕይወት ውኃ ምንጭ፡ የሕይወት ውኃ ምንጭ፡ ምን እንደሆነ ለማወቅ ችለናል? የውሃ ጉድጓድ ምን እንደሆነ አውቀናል፡ አሁን የሕይወት ውኃ ምንጭ ምንድ ነው? የምንጭ ውኃ ነው።

“ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ የምንጭ ውኃ፡ ምንድነው? ”

ሁልጊዜ ከሥር የሚፈልቅ ውኃውን ወደላይ የሚገፋ ሃይል ያለው ጉድጓድ ነው። ያለማቋረጥ ይፈሳል። በራሱ-የሚደገፍ ነው። የምንጭ ውሃ፡ ሁልጊዜ ፍሬሽ እና ንጹህ፡ የህይወት ውሃ ምንጭ ነው። የሞተና የተኛ አይደለም። ከምንጩ በመምጣት፡ ሁል ጊዜ አዲስ ነገር እያመጣ፡ የሚንቀሳቀስ፡ ያለማቋረጥ የሚቀየር፡ ህያው ምንጭ ነው። ከከርሰ ምድር—ምንጩን ይቀዳል፡ እሱም… እስካሁን የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ምንጭ ነው። ራሱን-የሚያነጻ፡ ንጹህ፡ ኩልል ያለ፡ ንጹህ ውሃ ነው። በራሱ-የሚደገፍ ነው፤ ታንከሩን ለመሙላት ዝናብ እስከሚዘንብ መጠበቅ አይጠበቅባችሁም። ሁሌም ወደላይ እየተፍለቀለቀ፡ ውኃ በነጻ ይሰጣል። ፓምፕ ማድረግ፡ ማሽከርከር፡ መጠምጠም፡ ወይም ማሰር አይጠበቅባችሁም። የህይወት ውሃ ምንጭ ነው።

75 ታውቃላችሁ፡ ለምሳሌ የድሮዎቹ ጉድጓዶች ብትወስዱ፡ ጥቂት የተኛ ውኃ ሰቦ ለማውጣት፡ ማዞር እና ማዞር እና ማዞር፡ ፓንፕ ማድረግ ልዩ ልዩ ነገር ማድረግ ይጠይቃል። ኧሃ!

የህይወት ውኃ ምንጭ ግን ያለ ፓምፕ፡ ያለ ማሰር፡ ያለ ምንም ነገር፡ በነጻ ይሰጣል። አቤቱ፡ ለሰዚያ ምንጭ ደሰ ይለኛል! አዎን፡ ወዳጄ!

76 ጥገኛ ታሕዋስያን ለማውጣት፡ በላዩ ምንም መጭመቂያ አያስፈልገውም። ከአለት ውስጥ፡ ከታች ስለሚወጣ፡ ጥገኛ ታሕዋስያን፡ አይገኙበትም።

መሰበክ መቻልህን፡ አለመቻልህን ከአእምሮ ሀኪም በፊት ሊነግርህ፡ አንዳንድ ወፍ-ዘራሽ የሰው-ሰራሽ የሃይማኖት ተቋም ጥበብ ሰርአት፤ ትምህርታዊ ጨርቅ፡ በላዩ ላይ ማንጠልጠል አይጠበቅበትም፡ ያ ትክክል ነው። በላዩ ላይ ከሚቀመጡ ከቆሻሻ ጨርቆች አንድም የለውም። በላዩ ላይ እንዳስቀመጣችሁበት ወዲያውኑ ገፍቶ ይጥለዋል። ያንን ማድረግ አትችሉም። ያ ምንጭ ሁልጊዜም፡ የሚፍለቅለቅ ነው። ከነዛ ጨርቆች አንዱን በላዩ ላይ ታረጉበታላችሁ፡ በአንድ በኩል ወይም በሌላ በኩል ወርውሮ ይጥለዋል። የሃይማኖት ተቋማዊ ጨርቅ በላዩ ላይ ለማድረግ ጊዜ የለውም።

77 ምንም ማጣሪያ፡ ምንም ማጥሊያ፡ ምንም ፓምፕ ማድረግ፡ ምንም መሳብ፡ ምንም ለላ ነገር ማድረግ አያስፈልገውም። እንዲሁ፡ ይፍለቀለቃል። ራሱን ለመሙላት በአከባቢው ዝናብ ላይ ጥገኛ መሆን አያስፈልገውም። **ዝናቦች** “ሪቫይቫሎች” ናቸው፡ ያ ምንጭ… በህይወት ምንጭ ላይ ነው። “ስጋ ባለበት፡ በዚያ ንስሮች ይሰበሰባሉ።” ተሃድሶን ፓምፕ ማድረግ የለባችሁም፡ ምንም ነገር ፓምፕ ማድረግ የለባችሁም። ማድረግ ያለባችሁ ብቸኛው ነገር ወደ ምንጩ መምጣት ብቻ ነው። ሁሌም በጥሩ ሁኔታ፡ በንጹህ ውኃ የተሞላ ነው፡ እና ማለቂያ የለውም። መፍለቀለቁን ይቀጥላል።

78 ወደ ጉድጓድ ሄዳችሁ፡ እንዲህ ማለት የለባችሁም፡ “እነሆ፡ ዝናብ ቢዘንብ ጎተራውንም ቢያጥብልን፡ የምንጠጣው ነገር ይኖረናል።” አያችሁ? ኦህ፡ ይገርማል! ይህን አይደለም። የምንጩ ውኃ ሁል ጊዜ ጥሩ፡ እና ቀዝቃዛ ውኃ ያመነጫልና። በእሱ መደገፍ ትችላላችሁ። እንዲህ ማለት የለባችሁም፡ “እነሆ፡ ወዳረጀው ጉድጓድ እሄዳለው። በፊት እንጠጣበት ነበር፡ ነገር ግን ለረጅም ጊዜ ዝናብ አልዘነበም። ምናልባት ደርቆ ይሆናል፡ እላችኋለሁ።”

79 ከእነዚህ ሰው-ሰራሽ ሰርዓቶች መካከል አንዳንዶቹ እንዲሁ ናቸው። ሄዳችሁ ስትገቡ፡ አንድ ትልቅ ነገር እየተካሄደ ከሆነ፡ የሆነ ነገር የሚሸጥበት ክምችት ይኖራል፡ ወይም—ወይም አንድዳንድ ነገሮች ይካሄዳሉ፡ ትልቅ ፓርቲዎች እና ሌሎች ነገሮች ይደረጋሉ፡ ቡንኮ ጨዋታዎች፡ የምድር ቤት ውስጥ ፓርቲዎች፡ ሌሎች ነገሮች፡ የሞላ ቤት ሊገጥማችሁ ይችላል።

ነገር ግን ምንጭ ወደሚፍለቅለቅበት በምትሄዱበት ቦታ፡ ሰዎች ሁሌም፡ ጥሩና ቀዝቃዛ፡ ውኃ ይጠጣሉ። ልትተማመኑበትም ትችላላችሁ! “ላለፉት አሰር ዓመታት ሪቫይቫል አልነበራቸውም፡” ትላላችሁ። በምንጩ የምትኖሩ ከሆናችሁ፡ ሪቫይቫል ሁሌም አላት።

80 ምስኪን ዌልሽማን እንዳለው። ወይም፡ በአንድ ወቅት የዌልሽ ሪቫይቫል በነበረ ጊዜ፡ ከዩናይትድ ስቴትስ የመጡ አንዳንድ ባለሥልጣናት ነበሩ። ከእነዚህ ታላላቅ የመለኮት ዶክተሮች መካከል አንዳንዶቹ፡ ይህ ሁሉ ሰለ ምን እንደሆነ እና የት እና ለማወቅ ወደ ዌልሽ ተጓዙ። ወደ ኋላቸው የዞረ-ኮሌታ እና ባርነጣቸውን ለብሰው፡ በየመንገዱ ላይ፡ ይመላለሱ ነበር።

እና አንድ ምስኪን ፖሊስ፡ በእጁ ትንሹን የራሱን አርጌውን የፖሊስ ዱላ እያሽከረከረ፡ እና እያፏጨ መጣ፡ “አዳኜ በሞተበት መስቀል ሥር፡ በዚያም ስለ ኃጢአት መንጻት ያለቀስኩበት፡ በዚያም ደሙ በልቤ ላይ ተረጨ፡ ክብር ለስሙ፡” እያለ ጎዳናው ላይ ይወርዳል።

እነሱም “ይህ ሰው ሃይማኖተኛ ይመስላል። ሄደን እንጠይቀው፡” ተባባሉ። እነርሱም “ጋሼ!” አሉት፡

እርሱም “አቤት፡ ዋዳጄ? ” አለ፡

እርሱም፡ “ከዩናይትድ ስቴትስ የመጣን ነን። የልዑካን ቡድን ነን። ወደዚህ የመጣነው የዌልሽን ሪቫይቫል ለመመርመር፡ ወዘ-ተረፈ ነው። የሥነ መለኰት ዶክተሮች ነን፡ እናም ለመመርመር መጥተናል።” “እኛ መነቃቃቱ የት እንደሆነ፡ እና የት እንደሚካሄድ ማወቅ እንፈልጋለን፡” አለ።

እርሱም፡ “የዌልሽ ሪቫይቫል እኔ ራሴ ነኝ። እነሆ፡ ደርሳችኋል።” አሜን! “የዌልሽ ሪቫይቫል በውስጤ ነው። ይህ እርሱ ያለበት ቦታ ነው።”

81 እንደዚህ ነው በዚያ በህይወት ውሃ ምንጭ ስትኖር። ደግሞ ደጋግሞ፡ እና በተደጋጋሚ፡ ሁል ጊዜም እየተፍለቀለቀ የሚኖር ነው። መጨርሻ የለውም። “እስኪ በቅርብ ጊዜ ዝናብብ የዘነብ ይመስለኛል፡ የተወሰነ ውኃ ካለ ወርዳችሁ ተመልከቱ፡” የሚባል አይደለም፡ አይደለም። እንዳልኳችሁ፡ ይህ የህይወት ውኃ ምንጭ ነው። ውኃውን በነጻ ይሰጣል።

82 በላዩ ላይ የማጣሪያ ጨርቅ ማድረግ አያስፈልጋችሁም፡ አንዳንድ ነገሮች ለማወቅ፤ ለሰብከት ከመላኩ በፊት፡ ቃላቶቹን በትክክል እንደሚል በትክክል እንደሚናገር ለማወቅ፡ አንዳንድ ትምህርታዊ ጨርቆች መደረብ አይጠበቅባችሁም፡ ሰሞችን እና ተውላጠ ሰሞችን እና ቅጽሎችን፡ እና የመሳሰሉትን፡ በአግባቡ ይጠቀማል ወይ። ብዙዎቹ እነዚህ ምን እንደሆኑ እንኳን አያውቁም፡ ሳይናወጥ ዝም ብሎ ምንጭ ላይ ይኖራል፡ አያችሁ፡ አይለዋወጥም።

83 እሱን ለመሙላት፡ በአከባቢው ዝናብ፡ ወይም በአከባቢው ሪቫይቫል ላይ፡ መደገፍ አያስፈልገውም። ኃይሉና ንጽህናው በራሱ ውስጥ ስለሆነ፡ ይህን

ማድረግ አያስፈልገውም። እነሆ የቃሉ መገኛም ይኸው ነው፡ በራሱ ኃይል! አንድ ሰው በልቡ ውስጥ እሱን ሊቀበለው ሲችል፡ ንፁህነቱን ያገኛል። ኃይሉን ያገኛል። የሕይወት ምንጭ የሚፈልቀው፡ በቃል ውስጥ ነው።

84 እስራኤል ከእርሱ ሲለዩ፡ ችግር ውስጥ ይወድቃሉ። በተለዩት ቊጥር፡ ችግር ውስጥ ይወድቃሉ።

አሁን ያለንበት ሁኔታም ተመሳሳይ ነው። እንደገና ሪቫይቫሉ ከዚያ ሲሸሽ፡ ያኔ ምንም አይጠቅምም። ለራሱ የሆነ ጉድጓድ ይቆፍራል፡ ወይም፡ የሆነ የተኛ ውሃ ያለበትን ጉድጓድ፡ እና በዚያው ይቀጥላል።

85 ይሁን እንጂ ሁልጊዜ ይረዳቸው ነበር። በቀይ ባህር ላይ ማጉረምረም፡ ከዚያም ሲያጉረመርሙ... ያም ሆኖ፡ በዛ ሁሉ፡ ቃል ገባላቸው፡ ቃል ክዳን አደረገ። እንደምንመለከተው፡ ወዲያው ሊያጠፋቸው ይገባ ነበር፡ ወደዚያ እንደሚወስዳቸው ግን ቃል ገብቶላቸው ነበረ።

ምን አደረገ? ስለ እስራኤል ልጆች፡ ያንን የእሳቱን አምድ እና ሌላው ሁሉ አዘጋጀላቸው፡ ይህም የነብያቸውን፡ ምስክር ለማቆም ነበረ። ወዲያውም ወደ ባሕር መሯቸው። እነሆ፡ ሁል ጊዜም፡ ተቃዋሚ ነበረበት። ፈርዖንና ሠራዊቱ መጡ። አምላክ ምን እንዳደረገ ታውቃላችሁ? የተኛው ቀይ የውኃ ጉድጓድን፡ ከፈተው።

የሙት ባሕር በዓለም ላይ እጅግ የሞተ ነገር ነው። በትክክል ሙት ነው። የተኛ ውኃ ነው። በውስጡ ሊኖር የሚችል ህይወት የለም።

እሱን ከፈተው እና በሌላኛው በኩል፡ ነጻ አወጣቸው። እንዲህ ባለ ነገር መታሰር ወደሌለባቸው ቦታ ወሰዳቸው።

86 በምድረ በዳ፡ ሊተማመኑባቸው የማይቻል ጉድጓዶች አገኙ፡ የደረቁ ነበሩ። ከአንዱ የውኃ ጉድጓድ ወደ ሌላው ሲሄዱ፡ ይታያሉ። በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ፡ ውኃ ለመጠጣት፡ በረሃብ ይሞቱ ነበር። ወደዚህ ወደ ውኃው ኩሬ፡ ይወርዳሉ፡ ደረቅ ነው። ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ፡ ያም ደረቅ ነው። ብቻ የሚጠጣ እንጠጣለን ብለው ማሰብ አቃታቸው።

ከዚያም በምድረ በዳ ሁሉም ባላሰቡበት ቦታ ላይ፡ ውኃን አገኙ። በዓለት ውስጥ። በዓለት ውስጥ ነበር። ሰው ምንም ውኃ ማግኘት በማይችልበት ቦታ፡ በምድረ በዳ መሃል በሚገኝ ደረቅ አለት ውስጥ ነው። ነገር ግን፡ አያችሁ። በጣም ባልተለመዱ ቦታዎች፡ በጣም ባልተለመደ መንገድ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ያሉ ነገሮችን ያደርጋል። ሁልጊዜ እንዲህ ያለ ነገር ያጋጥመናል።

87 ሪቫይቫል ለማድረግ፡ ትልልቅ የሃይማኖት ተቋሞች በአንድነት፡ ሁሉም አንድ ላይ ተሰብስበው እና ትልቅ ትርጉም የለሌው ጉባኤ፡ እና ልዩ ልዩ ነገር እንዲኖራቸው፡ ሺዎችም በአንድነት-እንዲያብሩ፡ **እንደዚህ** ያሉ ነገሮችን፡ ማድረግ አለብን ብለው ያስባሉ።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሀሁ እንኳን ያልቆጠረ ሰው መርጦ፡ ቀኝ እጃቸውን ከግራ እጃቸው ለይተው በማያውቁ መሃይሞች ጉባኤ መካከል፡ ዓለምን የሚያናውጥ ሪቫይቫል ሊያነሳ ይችላል። በዮሐንስ ዘመን እንዲሁ አድርጓል። በነቢያት ጊዜም አድርጓል። እንደምናውቀው፡ እንዳቸውም፡

የተማሩ አልነበሩም፡ እግዚአብሔር ግን እሱ ይዟቸው አንድ ነገር ሊያደርጉ አስችሏቸዋል።

88 ከዚህም ዓለት ላይ ውኃ ወጣ። እርሱ ራሱ ዓለት ነበርና። ይህንም ዓለት፡ ይመታ ዘንድ አዘዘ። እንዲሁም ለሚጠጡ ሁሉ ንጹሕ፡ ፍሬሽ፡ የጠራ፡ ውኃ አትረፍርፎ ሰጣቸው። ከዚያም የሚጠጡትን ሁሉ አዳናቸው። ከዮሐንስ 3:16 ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው።

> **... በእርሱ የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ፡... እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ፡ ግን** ዓለሙን **እንዲሁ ወዶአልና፡**

89 እግዚአብሔርም ያንን ዓለት፡ በቀራንዮ ላይ መታው። ለእኔ እና ለእናንተ ከእርሱ ዘንድ የሚመጣልን የዘላለም ሕይወት የሚሰጠን የሕይወት መንፈስ እናገኝ ዘንድ፡ ፍርዳችን በእርሱ ላይ ነበር። በዚህ ምድረ በዳ ውስጥ፡ ይህ ፍጹም የእርሱ ምሳሌ ነው።

90 መኰተት፡ መቆፈር፡ ፓምፕ ማድረግ፡ ሌላ ማንኛውንም ነገር ማድረግ አላስፈለጋቸውም፡ እሱ ያዘጋጀውን መንገድ ብቻ፡ በነጻነት ተካፍለዋል። ያን ጊዜ፡ ከኩሬ ውስጥ ለማውጣት መቆፈር አያስፈልጋቸውም። በባልዲ ጎትተው ማውጣት አያስፈልጋቸውም። እሱን ለማግኘት ምንም ገንዘብ ንብረት ማግኘት አያስፈልጋቸውም። በቃ መቋደስ ብቻ ነበረባቸው።

አሁንም ሊሆን የተገባው ይህ ነው። ምንም ነገር መቀላቀል አያስፈልጋችሁም። በመሠዊያው ላይ መውረድ እና አንድ ነገር መሥራት የለባችሁም፡ ፓምፕ ማድረግ የለባችሁም። የቋንቋ ግራ መጋባት እስኪያጋጥማችሁ ድረስ፡ አንድን ቃል ደጋግማችሁ ደጋግማችሁ መናገር አይገባችሁም። ማድረግ ያለባችሁ እሱን፡ በነጻነት ከሱ መቋደስ ነዉ፡ እግዚአብሔር የሰጠን መንገድ እሱ ነው። ፓምፕ ማድረግ፡ መግፋት፡ ምንም ነገር፤ አያስፈልግም፡ በነጻ ተቀበሉት። ምንም ማድረግ የለባችሁም፡ በቀላሉ ተቋደሱ። እንዲህ ነው፡ ብቻ እመኑት። ማለት የምችለው ይህ ብቻ ነው።

ለእሱ ምንም ነገር ማድረግ አልነበረባቸውም። ለእሱ መቆፈር በጭራሽ አላስፈለገም። በፍፁም ወደታች ወርደዉ ሌሊቱን ሙሉ ለእርሱ፡ ማልቀስ አልነበረባቸውም። እንዲሁ ተካፋይ ሆኑ፤ እሱም የተመታ እና የተዘጋጀ ነበር። ትክክል ነው።

91 እዚህ ክፍል ከኋላ ተቀምጦ፡ አሁን አንድ ሰው እየተመለከትኩት አለ። አንድ ቀን በግርግም አጠገብ፡ በአሮጌው የፈረሰ ማደሪያ ውስጥ፡ የነገርኩት ነገር አስታውሳለሁ።

እርሱም "እኔ ምንም የማልጠቅም ነኝ፡" አለኝ።

92 እኔም መለሰኩለት፡ "አዎን አውቃለው።" እኔም "እኔም ብሆን፡ አልጠቅምም፡" አልኩት። እኔ ግን "ማንነትህን እያየህ ስለሆንክ ነዉ። ማንነትህን መመልከት አቁም፡ እና እሱ ማን እንደሆነ ተመልከት፡" አልኩት።

"ወንድም ብራንሃም፡ እነዚህን ሲጋራዎች ማስወገድ ከቻልኩ፡ ክ—ክ— ክርስቲያን እሆናለሁ፡" አለኝ።

93 እኔም፡ "አታሰወግዳቸው። ጥሩ ከሆንክ በኋላ ወደ እርሱ ለመምጣት እየጣርክ ነው። መጥፎ መሆናቸውን የሚያውቁ መጥፎ ሰዎችን ሊያድን ነው እንጂ፡ ጥሩ ሰዎችን ለማዳን ፈጽሞ አልመጣም።"

እሱም "መልካም... " አለ፡

እኔም "ስማ፡ ወደ ሲኦል መሄድ አትፈልግም፡ አይደል? " አልኩት፡

እርሱም፡ "አልፈልግም" አለ።

94 እኔም፡ "መልካም፡ መሄድም አይገባህም። የሞተው አንተ ወደዛ እንዳትሄድ ነዉና።"

እርሱም "ምን ማድረግ አለብኝ? " አለኝ፡

እኔም "ምንም። እጅግ ቀላል ነው፡" አልኩት።

እርሱም "ግን ከቻልኩኝ... " አለኝ፡

95 እኔም፡ "እንዲህ አድርግ፡ ስለ ሰጋራው ማሰብን አቁም። ወደዚያ ሲጋራ ተመለስ። ብቻ ስለ እሱ፡ እሱ ያደረገውን ማሰብህን አትርሳ፡ አንተ ማን እንደሆንክ ሳይሆን፡ እሱ ማን እንደ ሆነ፡ አሰብ። አንተ ጥሩ አይደለህም፡ በጭራሽ አልነበርክም፡ በጭራሽ አትሆንምም። እርሱ ግን፡ መልካም ነው፡ ዋናውም እርሱ ነው!" እኔም አልኩት፡ "አሁን፡ ማድረግ ያለብህ አንድ ነገር ብቻ ነው፣ በፈንታህ ሰፍራህን እርሱ ከወሰደልህ፡ ያደረገውን በፊቃድህ ብቻ ተቀበል። ማድረግ ያለብህ ብቸኛው ነገር መቀበል ብቻ ነው።"

"እንዴ፡" አለኝ፡ "ያ'ማ ቀላል ነው። አደርጋለው።"

96 እኔም "እነሆ ውኃ፡" አልኩት። አያችሁ? ወደዚህ አምጥቼ በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም አጠመቅኩት።

ከወገኖቼ መካከል አንዳንዶቹ እዚህ ተቀምጠዋል፡ ያንን በማድረጌ በእኔ እንደሳቁብኝ አ—አውቃለሁ፡ ነገር ግን ምን እያደረግሁ እንደሆነ አውቅ ነበር። በሰውየው ውስጥ እውነተኛ የሆነ ነገር አይቼ ነበርና። ያን ነገር በዚያ ማየት ስለቻልኩ፡ ወሰጄ በጌታ በኢየሱስ ሰም አጠመቅኩት።

ያንን፡ እንዳደረግን፡ ወደ ልጁ ቤት ለመሄድ ብዙም አልቆየሁም። አንድ—አንድ ዛፍ የሆነ ቦታ ላይ ሲሰበር፡ እና ይህ ሰው ወድቆ፡ ጀርባውን ሲሰበር በራእይ አይቼ ነበርና። ወደ ሆሰፒታል ወሰዱት። በዛ ምሽትም፡ ጌታ ያ የሲጋራው መጨርሻ እንደሆነ፡ ገለጠልኝ።

ስለዚህ በነጋታው ሲጋራ ፈለገ። እኔም እንዲህ አልኩ፡ "ካርቶን ሙሉ ሲጋራ እገዛለታለሁ እና ውሰዱለት። ዝም ብላችሁ ተመልከቱ፡ የሲጋራው ቀናት አብቅተዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንዱንም አላጨሰም፡ እና ከዚያ በኋላ በጭራሽ አላማረውም። እግዚአብሔር ሆይ!

97 አያችሁ፡ መጀመሪያ ማድረግ ያለባችሁ ነገር ወደ ምንጩ መምጣት ነው። ወደዚያ ውኃ መምጣት አለባችሁ፡ እናንተ የምታደርጉት ምንም እንደሌለ ትገነዘባላችሁ። ዋናው ነገር እርሱ ለእናንተ ያደረገው ነገር ነው። መቆፈር፡ ፓምፕ ማድረግ አይጠበቅባችሁም፤ **ይህንን** መተው፡ **ያንን** መተው አያስፈልጋችሁም። ማድረግ ያለባችሁ በቸኛው ነገር ደርሳችሁ መጠጣት ብቻ ነዉ። ያ ነው በቃ። ከተጠማችሁ፡ ጠጡ!

98 አሁን፡ እርሱ አለት ነበር። እግዚአብሔር እርሱን ስለ እኛ መታው፡ እርሱም የተትረፈረፈ ንፁህ፡ የጠራ ውሃ ሰጠን። በዛሬው፡ ጊዜም ቢሆን፡ ለሚያምኑ ሁሉ ይህን ያደርግላቸዋል። ለእኛ፡ ለህዝቦቹ፡ ይህ ጸጋው ነው፡ በትክክል።

99 በዛሬው ጊዜ ያሉ ሰዎች፡ የሚያገኙትን ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ፡ ነገር ግን በምላሹ፡ ምንም ዓይነት አገልግሎት ለመሰጠት የማይፈልጉ ናቸው። እስራኤል አሁን ከዓለቱ ለ—ለመጠጣት ዝግጁ ነበር፡ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚገባውን አገልግሎት ለመሰጠት አልፈለጉም።

100 እርሱም ሁል ጊዜ ያገለግለናል። ታውቃላችሁ፡ ያለ እርሱ መተንፈስ እንኳን አንችልም። ያለ እግዚአብሔር አገልግሎት መተንፈስ አንችልም። ይህን ያህል በእርሱ የተደገፍን ነን። እናም፡ ገና፡ ለእርሱ የሆነ ነገር ለማድረግ ብንጥር፡ ለማድረግ ብንሞክር ለሁለት ይሰብረናል። የሆነ ነገር እንድናደርግለት ይፈልጋል፡ የሆነ ሰው እንድንጎበኝ፡ ለሆነ ሰው እንድንጸልይ፡ የሆነ ሰው እንድናግዝ፡ ይህን እንድናደርግለት፡ ይሰብረናል። እኛ ግን ስለ አገልግሎቱ ምንም ነገር ማድረግ አንፈልግም።

101 ወቀሳው፡ "እኔን ረሱኝ፡ ቃልን፡ በእኔ ፋንታም፡ የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶችን ተቀበሉ የሚል ነው። ተቀበሉ... የህይወት ምንጭ፡ የህይወት ውሃ ምንጭ፡ የሆንኩትን እኔን ረሱኝ፡ ይልቁን ግን ከተኛ ውኃ መጠጣት አሰኛቸው።" አሰባችሁታል?

102 አሁን አሰባችሁታል አንድ ሰው፡ ከበሃ ድንጋይ ውኃ ውስጥ፡ የሚፈልቅ ምንጭ፡ **እዚህ** ቢኖር፡ ልክ ከድንጋዮቹ ልብ፡ ከክምር አሸዋ ውስጥ፡ የሚወጣ፡ እንደሁኔታው ቀዝቃዛ እና መልካም የሆነ ውኃ እያለለት፡ ውኃን ለመጠጣት ከተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች፡ ከጉርኖ እጣቢ የተጠራቀመውን፡ ከጣራዎች፡ እና በዙርያ ካሉ-ህንጻዎች የወረደውን ይጠጣልን? የውኃው ፈሳሽ ወዲያው ወደሚፈሰሰበት፡ ወደዚያ ጓድጓድ ውስጥ ከሚተራቀምበት፡ ማለት ከዚያ ከጎተራ፡ ከበረት እና ጋጣዎች፡ የውኃ ጅረቶች እና ልዩ ልዩ ነገሮች ከሚፈሱበት፡ ከዚያም ለመጠቀም-... ምናልባት ወደ ምንጩ ከመሄዱ በፊት ከዚያ ውኃ ይጠጣልን? ያ ሰው ምናልባት የሰነ ልቦና ችግር ሊኖርበት ይችላል። ትክክል ነው።

103 ወንዶች እና ሴቶችም የሃይማኖት ተቋምን ሲቀበሉ፡ ማለት ፀጉር መቁረጥ፡ ቁምጣ መልበስ፡ ሜካፕ፡ እና ሌሎችንም ነገሮች ወደሚፈቅድ፡ እና የሆነ ት—ትንሽ ፕሮግራም፡ እና አንዳንድ ነገሮች የሚከናወኑባቸው፡ ወደ ቁማር ቤቶች፡ እና—እና ትርጉም ወደ ማይሰጡ ቦታዎች ሁሉ ይሄዳሉ፡ ያንን ሁሉም ይታገሳሉ፡ ይህም ያረጀ-ፋሽን ከሚሉት ከሚቆርጠው እና ከሚነቅለው ይልቅ ሴቶችን እመቤቶች ከሚያደርግ፡ በትክክል እንዲመላለሱ እና እንዲለብሱ ከሚያደርጋቸው፡ ሲጋራና ትምባሆ፡ መሃላና እርግማን፡ ውሸትና ሰርቆትን ሁሉ፡ ከላያቸው፡ ከሚያሰወግደው ይልቅ፡ እና ዓለምን ሁሉ ከእናንተ ዘንድ አሰወግዶ፡ ፍጹም የሆነውን ነገር ከሚሰጠው ይልቅ አብዝተው ይወዱታል። መጽናናትን ፍለጋ ወንድ ወይም ሴት እንዴት ወደዚያ አይነት ስፍራ ይሄዳል? ከዚያስ እንዴት መጽናናት ታገኛላችሁ?

104 ከተኛ ውኃስ ንጹህ የመጠጥ ውኃ እንዴት ታገኛላችሁ? እንዴት አንድ ሰው... እንግዲህ አንድ ሰው የተከፈተ ንጹህ የውኃ ምንጭ እያለ፡ ከተኛ የውኃ

ጉድጓድ ጋር ለመጠጣት ከሄደ፡ “ይህ ሰውዬ የአዕምሮ ችግር አለበት፡” ትላላችሁ።

እና ወንድ ወይም ሴት ምቾት ለማግኘት ወደ እንደዚያ አይነት ቦታ ከሄደ፡ ያ ሰው የሆነ መንፈሳዊ ችግር አለበት። ቃሉን አይፈልጉም። ስለዚህ ተፈጥሮአቸው አሁንም እንቁራሪት፡ ወይም ታድፖል፡ ወይም የሆነ ነገር፡ መሆናቸውን ያሳያል፡ በትክክል። የተኛ ውኃ የሚወድ ተፈጥሮ እንደሆነ ያሳያል፡ ምክኒያቱም እንደነዚህ ያሉ ነገሮች በንጹህ-ውኃ ውስጥ መኖር አይችሉም። መኖር አይችሉም፡ ንጹህ ውኃ ነው። መኖር አይችሉም።

105 አሁንም፡ ወቀሳው፡ “እሱን መተዋቸው ነው።” ዛሬም ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል።

አሁን ጉድጓዱ ጋር የነበረችውን ሴትዮ ተመለከቷት። መልካም፡ ወደ ያዕቆብ የውኃ ጉድጓድ ነው የመጣችው፡ ሁልጊዜ ከዚያ፡ ከያዕቆብ ጉድጓድ ውኃ ትቀዳ ነበር። የያዕቅብ ጉድጓድ ግን፡ የሃይማኖት ተቋም፡ ልንለው እንችላለን፡ ምክኒያቱም ሶስቱንም እሱ ቆፈራቸው፡ ይሄኛውም የቆፈረው ራሱ ነው። አሁን፡ እሷ ታላቅ ታሪክ ነበራት። እንዲህ አለች፡ “አሁን፡ አባታችን፡ ያዕቆብ ይህንን ጉድጓድ ቆፈረ። እሱም፡ ከብቶችም ሁሉ፡ ከዚህ ጉድጓድ ጠጥተዋል። ይህ አይበቃምን? ”

106 እሱም እንዲህ አላት፡ “ከዚህ ጉድጓድ የምትቀጅው ውኃ ግን፡ ዳግመኛ ይጠማሻል፡ ውኃ ለመቅዳት እንደገና መምጣት ይጠበቅብሻል። ነገር ግን፡” እንዲህ አለ፡ “እኔ የምሰጥሽ ውኃ ምንጭ ነው፡ ከውስጥ ምንጭ ይፈልቃልና፡ እሱን ለማግኘት ወደዚህ ሰፍራ መምጣት አይጠበቅብሽም። በአንቺ ውስጥ ይኖራል።”

107 ልብ በሉ። ስትጠባበቀው የነበረውን በመጽሐፍ የተጻፈውን ምልክት ባየች ጊዜ ግን፡ ማለትም የህይወት ምንጭ ሲያነጋግራት እንደነበር በገባት ጊዜ፡ ያንን የያዕቆብን የሃይማኖት ተቋም ትታው ሄደች እና እንደገና አልተመለሰችበትም፡ ምክንያቱም እውነተኛውን አለት አገኛታለች። አያችሁ? ወደ ከተማው ሮጠች። ኃጢአትን ተወች። ከእንግዲህ መጥፎ ሴት አይደለችም። እንዲህ አለች፡ “ኑ፡ ተመልከቱ ማንን እንዳገኘሁ፡ ያደረግኩትን በሙሉ የነገረኝ ሰው። እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? ” እ... ያ የውኃ ጉድጓድ መልካም ሊሆን ይችላል፡ የተፈጠረለትን ዓላማ አገልግሏል። አሁን ግን እሷ በትክክለኛው ምንጭ ነበረች። እውነተኛው ምንጭ እስኪከፈት ድረስ ያ የውኃው ጉድጓድ መልካም ነበር። እውነተኛው ምንጭ ሲገለጥ ግን፡ ጉድጓዱ ኃይሉን አጣ። ውኃ ለመጠጣት የተሻለ ቦታ እንዳለ ገባት።

108 የተሻለ ሰፍራ አለ። የተሻለ ሰፍራ አለ፡ እሱም በክርስቶስ ነው። በቅዱስ ዮሐንስ 7፡37 እና 38፡ ኢየሱስም ከበዓሉ በታላቁ በኋለኛው ቀን፡ እንዲህ አለ፡ “የተጠማ ቢኖር፡ ወደ እኔ ይምጣና፡ ይጠጣ።”

ሁሉም ደስ አላቸው። ከመሠዊያው በታች የሚፈልቅ ውኃ ወጣላቸው፡ እና የ—የበዓሉን መታሰቢያ በማድረግ፡ እነሆ ሁሉም፡ ሁሉም—ከዚያ ይጠጡ ነበር። ደግሞም “አባቶቻችን በበረሃ ከመንፈሳዊው ዓለት ጠጡ፡” በማለት ተናገሩ። አያችሁ፡ ለራሳቸው የውኃ ጉድጓድ ቆፍረው ነበር፡ ከሆነ ቦታ የሳቡት የተኛ ውኃ ነበራቸው፡ እናም እዚያ ከመቅደሱ በታች እንዲፈስ ያደርጉታል።

ሁሉም ተሰብስበው ከዚያ ውኃ እየጠጡ፡ “ከዘመናት በፊት፡ አባቶቻችን በምድረ በዳ ጠጡ፡” አሉት።

ኢየሱስም “በምድረ በዳ የነበረው ዓለት እኔ ነኝ፡” አላቸው።

“እግዚአብሔር ከሰማይ መና ሰጠን፡ እኛም በልተናል፡” አሉት።

109 “መናው እኔ ነኝ፡” አላቸው። እርሱ፡ ያ ምንጭ፡ በመካከላቸው ቆሞ ነበር። ያ የህይወት እንጀራ በመካከላቸው ቆሞ ነበር።

ቢሆንም አልፈለጉትም። ይልቅ የራሳቸው የውኃ ጉድጓድ እንዲኖራቸው ተመኙ፡ ምክኒያቱም፡ ሰው **ይሄኛውን** ሰራ፡ እግዚአብሔርም **ያንን** ላከ። ልዩነቱ ያ ነው። ለራሳቸው የውኃ ጉድጓድ ቆፈሩ!

110 እንዲህ አለ፡ “የተጠማ ቢኖር፡ ወደ እኔ ይምጣና፡ ይጠጣ፡” ምንጩ እሱ ነውና፡ “እና፡ መጽሐፍ እንዳለው፡ ከሆዱ የህይወት ውኃ ወንዝ ይፈልቃል።” ኦህ፡ የምንጭ ውኃ እርሱ ነው! “ከሆዱ፡” ወይም ከውስጥ ሰውነቱ፡ “የህይወት ውኃ ወንዝ ይፈልቃል።”

111 ያ ዓለት እርሱ ነው፡ እዚያ ውስጥ የነበረ... በችግሯ ጊዜ የደረሰላት፡ የአጋር ዓለት፤ ልጇ ለሞት በተቃረበ ጊዜ፡ ከግቢ ውጭ በተጣለችበት ጊዜ፡ ከብላቴናው እስማኤል ጋር ውጭ በነበረችበት ጊዜ የደረሰላት ዓለት እሱ ነው። ከጉድጓዷ ይዛ የወጣችው፡ የራሷ ውኃ፡ አልቆ ነበር። እና እስማኤልን አስቀመጠችውና፤ የፍላጻ ርቀት ያህል፡ ትንሽ ፈቀቅ አለች፡ እና አለቀሰች፡ ምክኒያቱም፡ አቤት፡ ልጇ ሲሞት ማየት አልፈለገችምና። በዛች ቅጽበት፡ የእግዚአብሔር መልአክ ተናገረ፡ እና ቤር-... ቤርሳቤህን አገኘች፡ እርሱም— የሚፈልቅ ምንጭ ነበር፡ እስከ ዛሬ ድረስም ይፈልቃል። የአጋር ቤር-ቤርሳቤህ ነበር፡ በዚያ በበረሃ የተገኘ ዓለት።

112 ያን ቀን፡ በደም ተሞልቶ በዚያ ምንጭ ዘንድ ቆሞ ነበረ፡ በቤተ መቅደሰ ቆሞ ነበር። [በቴፕ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... የአውሎ ነፋሰ ጊዜ። በትንቢተ ዘካሪያሰ 13ኛው ምዕራፍ፡ በዳዊት ቤት ዘንድ የተከፈተው ምንጭ እርሱ ነበር፡ ይህም ለማንጻት፡ እና (ከኃጥያት) ለማንጻት የተከፈተ። ያ ምንጭ ነው። በመዝሙረ ዳዊት 36፡9 ላይ፡ የዳዊት የህይወት ምንጭ ነበር። ዛሬም በዳዊት ቤት ምንጭ ነው።

የገጣሚው፡ በልቡ ውስጥ። ግጥሙ እንዲህ አለ፡

> በደም የተሞላ ምንጭ አለ፡
> ከአማኑኤል ደም ሰሮች የተቀዳ፡
> ኃጥያተኞች በፈሳሹ ሲጠልቁ፡
> የኃጥያት እድፈት ሁሉ ያነጻል።

የውኃ ምንጭ፡ የህይወት ምንጭ እሱ ነው። እሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

113 የመጨረሻው ዘመን ትውልዶች እርሱን፡ እውነተኛውን ቃል፡ የህይወት ውኃ ረስተውታል፤ ለራሳቸውም የሃይማኖት ተቋም ጉድጓድ ቆፈሩ፤ እና፡ እንደገናም፡ ፈለፈሉ፡ ቆፈሩ!

114 አሁንማ፡ የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች እንደነበሯቸው ገብቶናል። እነዚህ ጉድጓዶች በማያምኑ ጀርሞች፡ በእምነት አልባ ጉረኞች፡ በትምህርት

ፕሮግራሞች፡ እና በመሳሰሉት የተሞሉ ናቸው፡ ከእግዚአብሔር ኪዳን ጋር በሚቃረኑ ነገሮች የተመሉ ናቸው። የቃሉ ተጠራጣሪዎች ናቸው።

115 እንግዲህ፡ እነዚያ የነበሯቸው ጉድጓዶች፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፡ “የተቀደዱ” ይላቸዋል። **የተቀደደ** የውሃ ጉድጓድ “የሚያፈስ” ጉድጓድ ነው፡ እና ያንጠባጥባል። ምን ያደርጋል? የዓለም አብያተ ክርስትያናት ካውንስል ወደተባለው ማጠራቀሚያ ይንጠባጠባል። የተቀደደ የውኃ ገንዳ የሚመራቸውም ወደዚያ ነው፡ ይህም እሱን ስለረሱት ነው፡ ያን የህይወት ውሃ ምንጭ... ረስተው፡ ለራሳቸው እንዚህን ጉድጓዶች ስለሰሩ ነው።

116 ብዙ ታላላቅ የመማር ማስተማር ሴሚናር ሲስተሞችን፡ መቆፈር፡ እና ሌሎችም። ዛሬ ላይ የሚቆፍሩት እንደዛ አይነት ጉድጓድ ነው፡ ይህ ሰው እንዲሰብክ፡ ፒ ኤች. ዲ.፡ ወይም ኤል ኤል. ዲ.፡ ወይም ባችለር ድግሪ፡ ወይም የሆነ ደረጃ፡ ሊኖረው ይገባል ይላሉ። በሰው-ሰራሽ ቲኦሎጂ የተሞሉ የውሃ ጉድጓዶች። ወደነዚያ ታላላቅ ትምህርት ቤቶች ይወስዷቸውና፡ እዚያ የራሳቸውን ሰው-ሰራሽ ቲኦሎጂ ይከትቧቸውና፡ ያንን አስይዘው ይልኳቸዋል። አቤት እነዚያ፡ በሰው-ሰራሽ የውኃ ጉድጓዶች የቆየንባቸው ቀናቶች! ምን ችግር... ነገሩ መግማማቱ—አያስደንቅም፡ ኦህ፡ ማይ፡ ህዝቡም ከዚያ ስለሚጠጡበት ነው።

117 እና ዛሬ ሰዎች ደስታን ሲፈልጉ፡ ምን ያደርጋሉ? ሰዎች፡ የእግዚአብሔርን ደስታ ከመቀበል ይልቅ፡ ለደስታ፡ ወደ ኃጥያት ይዞራሉ። ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱ እና የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን የሚሉ ሰዎች፡ በእውነት ሲጨንቃቸው ሲጋራ ይሎኩሳሉ። እናም ትንሽ—ትንሽ ዘና ማለት ሲ—ሲያምርታቸው፡ ያልተገባ ልብሳቸውን ይለብሱና ወጥተው ወንዶች በሚያልፋበት፡ እንዲያፏጭላቸው ሳሩን ይቆርጣሉ። ታዋቂ ለመሆን ሁሉን ያደርጋሉ። እንደ ታዋቂ የፊልም ተዋናይ ለመታየት ይፈልጋሉ። ደስታቸው እሱ ነው።

ኢየሱስ፡ “እኔ በቂያቸው ነኝ፡” ባለ ጊዜ።

ወደዛ የሚሄዱበት ምክኒያት፡ ከምንጩ መጠጣት ስለማይፈልጉ ብቻ ነው። ውድቅ አድርገውታል። ከሱ መጠጣት አይፈልጉም። ራሳቸው ወደ ሰው-ሰራሽ ስርዓት ይቀላቀላሉ፡ የሆነ ብዙ የተኙ ነገሮች ያሉበት የውሃ ጉድጓድ፡ ወደዛ ሊሄዱ ይችላሉ።

118 ትላንት፡ ህጻናቱን ይዘን ወደ ወንዝ ወርደን ነበር። ቅዳሜ ጥዋት ይመስለኛል። ወደዚያ ወርደን ነበር፡ ቢሊ በጀልባ አሳ እያጠመደ ነበር። ህጻናቶቹንም ወሰድናቸው፡ ትንሹን የልጅ ልጄን እና ሌሎቹን፡ ሴት ልጄን፡ እና ትንሹን ልጄን፡ በጀልባ ለመንሸራሸር—ወደ ወንዙም ወረድን። በወንዙ ላይ በጀልባ መጓዝ እንኳን አትችሉም፡ እድፋም፡ ቆሻሻ፡ ወፈፌ ሰዎች እርቃናቸውን በወንዙ ዙሪያ ከመኖራቸው የተነሳ፡ መቅዘፍ አይቻልም። አንድ ጀልባ በአጠገባችን እያለፈ፡ የአስራ ሁለት-፡ የአስራ አራት-ዓመት-እድሜ ያላቸው ወንድ ልጆች፡ በእጃቸው የቢራ ጠርሙስ፡ እና ሲጋራ የዘው ነበር። እሱን “መዝናናት፡” ይሉታል። ኦህ፡ ይገርማል! ይህ ዓለም በእንደዚህ ዓይነት ስርዓት፡ ምን ያህል ይቆይ ይሆን?

119 ከዛም ሲሞቱ ወደ ሲኦል ከመሄድ ሃሳብ ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት፡ ከእነዚህ ሰው-ሰራሽ ጉድጓዶች መካከል፡ ወደ አንዱ ይሄዳሉ። ስለዚህ እዛው

የውኃው ጉድጓድ ውስጥ ተመሳሳይ ሰዎች ናቸው ያሉት። ብዙ የዓለም ርኩሰት፡ የቆሸሹ ዊግል-ቴይሎች ከመሆን የዘለሉ አይደሉም። ከሰርአቱ ጋር ይጣበቃሉ ምክኒያቱም፡ አሮጊትዋ እናቴ “ባለ ተመሳሳይ ላባ ወፎች አብረው ይበራሉ፡” ትል ነበር። ወደ ምንጩ መጥተው ህይወታቸው ከኃጥያት መንጻት አይፈልጉም። ከዚያ ውጭ ለመኖር እየተመኙ፡ ክርስትያን ስለመሆናቸው ይመሰክራሉ። ለምን? እውነተኛው የደስታ፡ የህይወት ምንጭ፡ የተሟላ ህይወት እና እርካታ ከሆነው፡ ከእርሱ ፈቀቅ ብለዋል። ያን ያደረጉበት ምክኒያት፡ መቀላቀል ስለሚፈልጉ ነው። በእነዚያ ነገሮች የሚያምኑ ዓይነት ሰዎች በመካከላቸው ናቸው።

120 በቅርብ ጊዜ፡ እኔና ወንድም ፍሬድ፡ እና ወንድም ቶም፡ ከሌሎች ወንድሞች ጋር በቱሰን ከተማ ታዋቂ ወደሆነ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ሄደን ነበር፡ ምናልባት አዲስ ስሜት እንዲሰማን የሚያደርግ ነገር ካገኘን ብለን ነበር የሄድነው። አገልጋዩም በግብጽ ስለነበሩ ሰዎች የሆነ ነገር ተናገረ፡ ከግብጽ በወጡ ጊዜ ሽንኩርት እና የመሰሉትን ይመገቡ ነበር፡ ያንን ለመመገብ ወደዚያ መመለስ ፈለጉ። እንዲህ አለ፡ “የዛሬ ሰውም ልክ እንደዚህ ነው።”

እና፡ ሁላችንም፡ “አሜን!” አልን፡ እንደዛ ዓይነት የህዝብ ብዛት አይቼ አላውቅም! መላው ቤተ ክርስቲያን ሰባኪውን ማየት ትተው “አሜን” ያሉትን ለማየት ወደኋላ ዞሩ። ምን እንደሆነ አልገባቸውም ነበርና። እስከ ሞት ድረስ እጅግ አሰደነገጣቸው።

ዳዊት፡ እንዲህ ባለ ጊዜ፡ “የደስታን ድምጽ ለእግዚአብሔር አሰሙ። በበገናም አመስግኑት! በጸናጽል አመስግኑት! እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን። እግዚአብሔርን አመስኑት!” እግዚአብሔር በህዝቡ ደስ ይሰኛል። ትክክል የሆነ ነገር በተነገረ ቁጥር፡ ነገሩን የተረዱ ሰዎች ”አሜን፡” ይበሉ።

121 ለምንድነው ከዚህ ዓለም ሰርዓት እና ጉድጓድ ተመልሰው፡ ወደ ታመነው የእግዚአብሔር ሰርዓት፡ ምንጭ ወደ ሆነው፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የማይመለሱት? እግዚአብሔር የተትረፈረፈ ደስታችን ነውና፡ ወደ እርሱ ስለ ምን አትመለሱም፡ በምስጋና ውስጥ፡ የተትረፈረፈ እርካታ ወደሚሰጥበት ለምን አትመለሱም? የነርሾቼ እርጋታ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

ጉድለት በተሰማኝ ጊዜ፡ እርካታዬን በክርስቶስ አገኛለው፡ ሲጋራ ውስጥ አይደለም፡ በአለም ነገሮች አይደለም፡ የሆነ የሃይማኖት መገለጫ በመቀላቀል አይደለም፡ ነገር ግን እሱን በማግኘት፡ በገባልን ቃልኪዳን መሰረት፡ “እኔ ብሄድ፡ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለው።” ደስታዬን የማገኘው በዚህ ውስጥ ነው። እሱ ደስታዬ ነው።

122 ዛሬ እንደዚህ ይላሉ፡ እነዚህን ነገሮች በመቀላቀል እና አለም የአቀፍ አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል በመስራት፡ ለመኖር ምቹ ሰፍራ እንፈጥራለን ይላሉ። በርግጠኝነት የሚሰማኝ፡ ኃጥያት ለመስራት ምቹ ሰፍራ ሊሰሩ እንደሆነ ነው። ያ ማለት... ሙሉ በሙሉ ኃጥያት ነው፡ ለማንኛውም፡ ለህይወት ሳይሆን፡ ለሞት ነው። ከህይወት ይልቅ፡ ለሞት ቦታ ያዘጋጃል።

123 ከኢየሱስ ክርስቶስ እና ከህይወት ቃሉ ውጭ፡ ሁሉም ነገር፡ የተቀደደ የውሃ ጉድጓድ ነው። እርሱን ለመተካት የሚሞክር ማንኛውም ነገር፡ ሰላም

እንዲሰጣችሁ ለማድረግ የምትሞክሩት ማንኛውም ነገር፡ ምቾት እንዲሰጣችሁ ለማድረግ የምትሞክሩት ማንኛውም ነገር፡ ከሌላ ከምንም ነገር የምታገኙት ደስታ፡ እርሱን የተካ ማንኛውም ነገር፡ እሱ ቆሻሻ የሞላበት የተቀደደ የውኃ ጉድጓድ ነው። ፍጹም እርካታ የሚሰጥ እርሱ ነው።

124 አስታውሳለው እዚህ ቦታ፡ ከሁለት የክረምቶች በፊት፡ በጀርባ በር ወጣሁና። በዚያም አንድ ወጠጤ ወጣት ነበረና እንዲህ አለኝ፡ "አጫጭር ልብሶችን እና መሳይ ነገሮችን የሚለብሱትን ሴቶች፡ የምትናገራቸው፡ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ፡" አለኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ "ምክኒያቱም አንተ ሽማግሌ ነህ።" "ምክንያቱ ይህ ነው፡" አለኝ።

"ይኸውልኽ። ስንት ዓምትህ ነው፡" ብዬ ጠየቅኩት?

"ሃያ-ሰባት፡" አለኝ።

125 "በእድሜ ከአንተ በጣም በማንሰበት ጊዜም፡ ሰብከቴ ያው ነበረ፡" አልኩት።

የእርካታን ምንጭ አግኝቻለው። እርሱ እጣ ፈንታዬ ነው። አሜን! እሱ ያን እስካቀረበልኝ ድረስ፡ ውበቱ ያ ነው። ያ—ያ የእኔ... ጥበቤ፡ እርሱን ማየት ነው፡ እጁ ስትሰራ መመልከት። ሌላ ምንጭ እኔ አላውቅም!

ኡህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ፡
ኃጢአቴን ያጠበው፤
ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

በደም የተሞላ ምንጭ አለ፡
ከአማኑኤል የደም ስሮች የተቀዳ፡
ኃጥያተኞች በምንጩ ሲጠልቁ፡
የኃጥያት እድፈት ሁሉ ያነጻል።

126 እነግራችኋለው፡ እኔ ከዛ ምንጭ ሌላ የማውቀው ምንጭ የለም። ቆሽሼ በነበረበት ጊዜ አነጻኝ። ንጹህ ያደርገኛል፡ ምክኒያቱም እኔ በእሱ መኖር ፈልጋለው፡ ነፍሴን በደስታ የሚሞላኝን ያን ንጹህ ውኃ መጠጣት ፈልጋለው።

በጣም ወድቄ ልሆን ይችላል፡ ፈጽሞ መቀጠል እንደማልችል ሊሰማኝ ይችላል... ከእንግዲህ፡ የትም መቀጠል እንደማልችል ሲሰማኝ፤ ይልቅ በጉልበቴ ተንበርክኬ እጄን በቃልኪዳኑ ላይ አድርጌ፡ እንዲህ እላለው፡ "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ አንተ ኃይሌ ነህ። አንተ እርካታዬ ነህ። አንተ ለእኔ ሁሉ-በ-ሁሉ ነህ።" ያኔ የሆነ ነገር በውስጤ ሲፍለቀለቅ ሊሰማኝ ይጀምራል። ከዛ እወጣለሁ።

127 እድሜዬ ሃምሳ እንዳለፈ መጠን፡ በማለዳ እነቃለሁ፡ እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ አንድ እግራችሁ እንኳን ከአልጋ ላይ ማውረድ አትችሉም። አቤት፡ ፈጽሞ አትችሉም፤ እና የሆነ ሰው በር ላይ፡ ያንኳኳል፡ ወይም ቢሊ አስቸኳይ ጉዳይ እንዳለ፡ መሄድ ያለብኝ ቦታ እንዳለ ይነግረኛል። አንድ እግሬን ለማውረድ እያሰብኩኝ፡ "እንዴት አደርገዋለሁ? " ብዬ አስባለው።

እንዲህ አስባለሁ፡ "አንተ የኃይሌ ምንጭ ነህ። አሜን! ኃይሌ እና ረድኤቴ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። አንተ ምንጩ ነህ! አንተ ወጣትነቴ ነህ!

'እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ኃይላቸውን ያድሳሉ፡ እንደንስር በክንፍ ይወጣሉ፣ ይሮጣሉ አይታክቱም፡ ይሄዳሉ፡ አይወድቁም።' ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ መሄድ፡ ግዴታዬ ነው። ለግዳጅ ተጠርቻለሁና።" እና ታውቃላችሁ በመጀመሪያ፡ የሆነ ነገር በውስጤ ይጎተጉተኝ ይጀምራል።

128 ባለፈው ቀን፡ ካንሳስ ውስጥ፡ ቶፔካ ላይ፡ አነስ ባለች ቦታ ውስጥ ስብሰባ እያረኩ ነበር፡ በዚያም፡ ወጣት ሰባኪ ነበረ፡ ከመጀመሪያዎቹ ስፖንሰሮቼ አንዱ ነበር። እዚያ ቁጭ ያለው፡ ወንድም ሮይ፡ ቦታውን ያስታውሰዋል። በዚህ፡ በዚህ ታላቅ ሰፍራ፡ አ—አንድ ነገር ነበረ... አንድ አገልጋይ ግድግዳው በጎን በኩል ወድቆበት፡ ከጣሪያ ወይም ከሆነ ቦታ ስር ወድቆ ነበር። ምስኪን ሰው ሞት አፋፍ ላይ ነበር። ጉበቱ ተሰንጥቆ። ጣፍያው ቦታውን ለቆ ነበር። በጣም ትልቅ ክብደት ያለው ነገር ወድቆበት ነበርና።

129 ቁርስ ላይ፡ ከምስቴ ጋር እያወራን ነበር። እንዲህ አልኳት፡ "ሚስቴ፡ ታውቂያለሽ፡ ኢየሱስ እዚህ ቢኖር ኖሮ፡ ምን እንደሚያደርግ ታውቂያለሽ? " አልኳት፡ "እኔን ስፖንሰር ሲያደርግ፡ ክርስቶስን ስፖንሰር እያደረገ እንደነበረ 'ቃሉን አምነዋለሁ።'" እንዲህ አልኳት፡ "ይህ የዲያብሎስ ማታለያ ነው።" አልኳትም፡ "ኢየሱስ እዚህ ቢኖር ኖሮ፡ ሄዶ የተቀደሱ እጆቹን በላዩ ይጭንበት ነበር። ልጁም በዳነ ነበር። ጉበቱ ቢፈነዳም ግድ የለኝም። በዳነ ነበር፡ ምክኒያቱም ኢየሱስ ማን እንደነበረ እያወቀ ወደዚያ መሄዱ አይቀርም ነበርና። ጥሪውን ያውቃል፡ ቅዱሳት መጽሐፍት ትክክል ናቸው፡ በእርሱ እንደተረጋገጠ እርሱ ማን እንደነበረ ያውቀዋል፡ ማለት ያለ... አንዳች ጥርጣሬ። እጁን ጭኖበት፡ 'ልጄ ሆይ፡ ተፈወስ፡ ከዚያ ውጣ፡' ባለው ነበረ።" እኔም እንዲህ አልኩኝ፡ "እንግዲያውስ፡ ወጣቱን መግደል የሚችሉ በቂ ሰይጣኖች በሲኦል ላይ አይኖሩም። ደና ይሆናል፡" አልኩኝ። እኔ ግን "አየሽ፡ ማርዬ፡ እርሱ ኢየሱስ ነው፡ የእግዚአብሔር ቅዱሳን እጆች ናቸው፡" አልኳት።

አልኩኝ፡ "እኔ ኃጢአተኛ ነኝ። አወላለዴም ከወንድ ፈቃድ ነው። አባቴና እናቴ ኃጥያተኞች ነበሩ፡ እኔም የከንቱ-ከንቱ ምንም ነኝ።"

እኔም አልኳት፡ "ግን ታውቂያለሽ? ጌታ ራእይ ቢያሳየኝ እና ሂድ ብሎ ቢልከኝ ግን፡ ያኔ ነገሩ ሌላ ይሆን ነበር።" "ወርጄ እጄን በእሱ ላይ በጫንኩ ነበር። ራእይ ቢያሳየኝ ኖሮ ከአልጋው ላይ በወጣ ነበር፡" አልኳት።

130 ከዚያም ማሰብ ጀመርኩ፡ "ለመሆኑ፡ ራእዩ ቢሆንስ፡ ምን ለውጥ አለው? እጆቼም ቢሆኑ ያው የቆሸሹ ናቸው። ኡህ-ሁህ፡ ያው ሰው፡ ያው የቆሸሹ እጆች ይጸልዩለታል።"

ከዛ፡ "እኔ የእሱ ተወካይ ነኝ ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር እኔን አያየኝም። በመሠዊያው ላይ በዚያ ያለው የጻድቁ ደም፡ እነሆ እርሱ ይማልዳል። እሱ በቂዬ ነው። እርሱ ጸሎቴ ነው። እርሱ ሕይወቴ ነው።" እንዲህ አልኳት፡ "እጄን በእርሱ ላይ እንድጭን የሚያደርገኝ፡ በራእዩ ላይ እምነት ስለነበረኝ ነው፡ በእምነት ነው። ያለ ራእይ ቢሆንም፡ ያው እምነት ያንኑ ነገር ያደርጋል፤ ስለዚህ ለራሴ ምንም ነገር ልቆጥር አልችልም፡እሱን ግን ለእኔ ሁሉ-በ-ሁሉ ነው። እሱ ህይወቴ ነው። እሱ አዛዤ ነው። የሃይማኖት ተቋም አላከኝም፡ የላከኝ እርሱ ነው። ሃሌሉያ! በስሙ እሄዳለው። እጄን እዘረጋበታለሁ።"

ወደዚያ ወርጄ ልጅ እጄን ጫንኩበት፡ እና በዚያ ምሽት ጤነኛ ሆኖ፡ ጉባኤው ላይ ተገኘ። አሜን!

131 ኦህ፡ አዎን፡ እርሱ ያ ምንጭ ነው። "ሌላ የማውቀው ምንጭ የለም። የክርስቶስ ደም ብቻ ነው!" እኔም ብሆን ሁላችንም፡ አንረባም፡ ጠረናችን ክፉ ነው፡ በእግዚአብሔር ፊት ግን ፍፁማን ነን። ኢየ-... "የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ፡ ፍጹማን ሁኑ።" እንዴት ልትሆኑ ትችላላችሁ? ምክኒያቱም በዚያ የሚወክለን ፍጹም ነውና። ምንጩ በዚያ ሁልጊዜ፡ ንጹህ ነው። የተኛ ውኃ አይነት አይደለም፡ ዘወትር ግን ንጹህ፡ ኃጥያቴን ሁሉ የሚያጥብ። እርሱ ያው ምንጭ ነው።

132 አሁን በመዝጊያ ላይ፡ ይህን ልናገር። ከዚህ የተለየ ማንኛውም ነገር የተቀደዱ ጉድጓዶች ናቸው፡ በዚያም የምታደርጉት ነገር ሁሉ ያፈሳል፡ ጊዜአችሁ ሁሉ፡ ተስፋችሁን በሙሉ፡ እና ሁሉንም ነገር፡ በተኙት ጉድጓዶች የምታደርጉ ከሆናችሁ መንጠባጠቡ አይቀርም፣ ኢየሱስ የተቀደዱ ጉድጓዶች እንደሆኑ ተናግሯል። እግዚአብሔርም አለ፡ "የተቀደዱ ስለሆኑ፡ የትጨምሩት ሁሉ ይፈሳል።" ስለሚያፈሱ፡ አብራችሁ ብዙ መጓዝ አትችሉም። ወደ እውነት፡ ወደ ህይወት፡ እና ወደ ዘላለማዊ ሰላም፡ የሚወስደው መንገድ እርሱ ብቻ ነውና። ወደዚያ የሚወሰደው ብቸኛው እና ብቸኛው መንገድ እርሱ ብቻ ነው። ኦህ፡ ይገርማል!

133 የማያልቅ የሕይወት ምንጭ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለምን? እሱስ ማን ነው? ቃል፡ ያው፡ ቃል፡ ህይወት፡ ምንጭ፡ "ትላንትናም፡ ዛሬም፡ እስከዘላለምም ያው ነው።" እውነተኛ አማኝ፡ ከሁሉ የላቀ ደስታ፡ የበላይ ሕይወቱ ነው። ከፍተኛ እርካታውም በክርስቶስ ነው። ምንም ጉተታ የለውም፡ መሳብ የለውም፡ መቀላቀል የለም፡ ዋሰ መሆን የለም፡ ማመን እና ማረፍ ብቻ ነው። እርሱ ለሚያምኑ እንዲህ ነው።

134 ልክ እንደ አባታችን አብርሃም፡ እርሱ በፍጹም ጎትቶ፡ ፈርቶም፡ ተጨንቆም አያውቅም። ቃል ነበረውና። በኤልሻዳይ ጡቶች መሃል ላይ ተደገፏልና። አብርሃም መቶ ዓመት ሲሆነው፡ እግዚአብሔር ተገለጠለትና፡ "እኔ ሁሉን ቻይ ነኝ፡" አለው። የዕብራይስጡ ቃል **ኤል ሻዳይ** ይላል፡ ትርጉሙም፡ "ጡት-ያለው፡" ማለት ነው። "አርጅተሃል፡ ኃይልህ የለም፡ ከእቅፌ ገብተህ ኃይልህን ከዚህ ምንጭ ጠግን።" አሜን! ጠብቶ ምን አገኘ? አዲስ ሰውነት። ከሣራ፡ ልጅ ወለደ። እና፡ ከሃምሳ ዓመታት በኋላ፡ ከሌላ ሴት ሰባት ልጆች ወለደ።

135 ኦህ፡ ኤልሻዳይ! ብሉይ ኪዳን ያኔ ያደረገውን ያሳያል፡ አዲስ ኪዳን ሊያደርገው ያለውን ይናገራል። አሜን! በብሉይ ኪዳን...

136 አሁን አየሩ ሰለጠፋ፡ አሁን እፈጥናለሁ፡ በደቂቃዎች ውስጥ እዚህ ጋር አቆማለሁ።

ከመዝጋቴ በፊት ይህን ማለት እፈልጋለሁ። አንድ ጊዜ ለዚህ የሚሆን ጥሩ ምሳሌ ገጠመኝ። እየዞርኩ ነበር። እና እዚህ በጆርጅታውን ዙሪያ፡ ብዙ ሰዎች... በሚሊታውን ውስጥ፡ ከኮረብታው፡ ወዲያ ማዶ፡ ምንጭ ነበር። የምንጭ ውኃ ነበር። አራት- ወይም አ—አምስት-ጫማ ርዝመት ያህል የውኃ ጅረት ይወርዳል፡ ሁል ጊዜ ይፈሳል፡ እና በአከባቢው ላይ ትልቅ ምንጭ ነበር። እና በዙሪያው ብዙ የሜንታ አበባዎች ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ በዚያ ዳር፡ ሚንት-መሳይ ነገሮች

ይበቅላሉ። እና፡ አቤት፡ ብቻ ወደዚያ ለመድረስ፡ ኦህ፡ ማይ፡ ወደ ምንጭ ለመድረስ እጠማ ነበር። እና ጋደም እልና ጥጥቼ ጠጥቼ፡ ቁጭ እልና ደግሞ እጠጣለሁ፡ እጠብቃለው።

እና ከዓመት ወደ ዓመት አሁንም ወደዚህ ምንጭ እመጣለሁ። ክረምትም ሆነ በጋ፡ አቋርጬ አላውቅም። ማብረድ አልቻሉም። የምንጭ ውሃ ማብረድ አትችሉም። ኦህ፡ በፍጹም! ኦህ፡ በፍጹም! እንዴትም—እንዴትም ቢቀዘቅዝ ግድ የለኝም፡ በረዶ ሊሆን አይችልም። የጉድጓድ ውኃ ግን በረዶ ማድረግ ትችላላችሁ፡ ትንሽ ትንሽ ነገር በረዶ ያደርገዋል። አያችሁ?

ነገር ግን የሚንቀሳቀስ ነገር፡ በውስጡ ሕይወትን የያዘ ነገር፡ ይንቀሳቀሳልና። ስለዚህ የምንጭ ውኃ ማብረድ አትችሉም። የአካባቢው መንፈስ ምንም ቢታወክ እንኳ፡ ምንጭ ሁል ጊዜ በሕይወት ይኖራል። እናንተም በምንጩ ኑሩ።

137 እስታውሳለሁ፡ እሄድና እጠጣበታለሁ፡ እና፡ አቤት፡ ይገርማል፡ ንጹህ ውኃ! “ወደዚያ ስሄድ፡ ምንጩ ይቆም ይሆን? ብላችሁ አትጨነቁም፡” ሁሌ እንደፈሰሰ ነው፡ መቼም ቢሆን መጨነቅ የለባችሁም…

138 አንድ አዛውንት ገበሬም “አያቴ ይጠጣበት ነበር፡” ብሎ ነግሮኝ ነበር። እና “በፍጹም አልቀነሰም ወይም ምንም አልሆነም። አሁንም እንደ ድሮው፡ ወደ ብሉ ወንዝ የሚንዶለደል ምንጭ ነው፡” አለ።

139 እኔም “አቤት፡ ይገርማል፡ ለመጠጣት እንዴት ይመቻል!” ብዬ አሰብኩኝ፡ ወደዚያ ለመድረስ፡ ከመንገድ አንድ ማይል ያህል እራመድ ነበር፡ ምክኒያቱም ለመጠጣት ምቹ ቦታ ነበር። ኦህ፡ ውኃው እንዴት ጥሩ ነው! ኦህ፡ ይገርማል!

እዚያ—በአሪዞና፡ ባለው ምድረ በዳ ሆኜ፡ አሁንም ስለእሱ አስባለሁ፡ “ወደዚያ ድንቅ ምንጭ ጉድጓድ፡ መውረድ ብችል እላለሁ!”

ዳዊት አንድ ጊዜ እንደተናገረው፡ “ኦህ፡ ከዚያ ጉድጓድ አንድ ጊዜ በጠጣሁ!” መግባት ቢችል ተመኘ!

140 እናም አንድ ጊዜ በዚያ ተቀምጬ፡ ትንሽ አስቂኝ ነገር ገጥሞኝ ያውቃል። እንዲህ አልኩት፡ “እንዲህ ሁል ጊዜ የሚያስደስትህ ምንድነው? እንዲሁ እኔም ደስተኛ በሆንኩ እልኩ። ለምን፡ ወደዚህ መምጣት ከጀመርኩ ወዲህ፡ አንድም ቀን አዝነህ አይቼህ አላውቅም። አንድም ቀን አዝነህ አታውቅም።” እንዲህ አልኩ፡ “ሁልጊዜ በደስታ የተሞላህ ነህ። ትዘላለህ ትፈነድቃለህ ትሄዳለህ። ክረምትም ሆነ በጋ፡ ሙቅ ሆነም ቀዝቃዛ፡ ምንም ይሁን፡ ሁልጊዜ በደስታ ትሞላለህ። ምንድነው… ? ምንድነው፡ እሱ? ከአንተ ስለጠጣሁብህ ነውን? ”

“አይ።”

“መልካም፡ ምናልባት ጥንቸሎች ካንተ ይጠጡ ይሆናል፡ አንተም ደስ ይለሃል፡” አልኩ።

“አይ።”

“እንግድህ፡ እንደዚህ እንድትፈነዳ ያደረገህ ምንድነው? በጣም የሚያስደስትህ ምንድነው? ሁልጊዜ በደስታ የሚሞላህ ምንድነው፡” ብዬ ጠየቅኩት? “ወፎች ከአንተ ስለ—ስለሚጠጡ ነውን፡” አልኩት?

“አይ።”

“እኔ ከአንተ ስለምጠጣ ነውን? ”

“አይ።”

“እሺ፡ ምንድነው በደስታ የሞላህ፡” አልኩት?

141 እና ምንጩ ሊመልስልኝ ቢችል ኖሮ፡ እንዲህ ይለኝ ነበር፡- “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በርግጥ መጠጣትህ አደንቃለሁ፡ አንተ ስለጠጣህ፡ ወይም ወፎችን ስለማረካ አይደለም። መጠጣት ለሚፈልግ ማንኛውም አካል አረካለሁ። ከአንተ የሚጠበቀው መጥተህ መጠጣት ብቻ ነው። እንዲህ የሚያስደስተኝ፡ ግን፡ የምፈነድቀው በራሴ አይደለሁም፡ ከውስጤ፡ የሚገፈትረኝ ኃይል አለ፡ የሚያስፈነድቀኝ ነገር አለ።”

142 በመንፈስ-የተሞላ ሕይወትም እንደሁ ነው። ኢየሱስ እንደተናገረው፡ በዚያም እንደነበረ... እያችሁ፡ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጮች ይሰጣችኋል፡ የማያቋርጥ ምንጭ፡ ሳያቋርጥ የሚፈስ ጅረት። ሌላው የቤተ ክርስቲያን አካል ከፍም አለ ዝቅ፡ አንተ ያው ምንጭ ነው።

ወደማያቋርጥ ምንጭ ተጠርታችሁ ሳላችሁ፡ ጥገኛ ታሕዋስያን እና ሌላ ነገሮች የተሞላውን፡ ያረጀ የሃይማኖት ተቋም ስራዓት እና ጉድጓድ ለምን ትመኛላችሁ፡ ለምንስ የተኛውን ነገር መጠጣት ያምራችኋል?

143 እንዴት እንደሚገፉ፡ እና እንደሚወነጨፍ፡ እና እንደ––እንደሚጎረጉር፡ እና እንደሚሰቅ፡ እና እንደሚዘል፡ እና እንደሚፈነጥዝ፡ አሰባለው። ቀዝቃዛ፡ ዝናባማ፡ ሞቃት፡ ደረቅ፡ ሌላው የሀገሪቱ ክፍል በሙሉ ሲደርቅ፡ እሱ ግን ሁልጊዜ ይፈልቃል። ምክኒያቱም ከሚወጣበት ዓለት፡ ጥልቅ ሥር፡ ዘልቆ የገባ ነውና።

144 ኦህ፡ በጅረቱ አጠገብ ልኑር! እናንተ የፈለጋችሁትን ሰው-ሰራሽ ስርዓት፡ የተኙ የውኃ ጉድጓዶች ውሰዱ፡ ወይም የተኙ ጉድጓዶችን፡ እኔ ግን፡ ወደ... ምንጩ ልምጣ፡ እሱ ወደ ሞላበት ብቻ ልምጣ። እሱ ደስታዬ ነው። እሱ ብርሃኔ ነው። እሱ––እሱ ኃይሌ ነው። እሱ ውኃዬ ነው። እሱ ህይወቴ ነው። እሱ ፈዋሼ ነው። እሱ አዳኜ ነው። እሱ ንጉሴ ነው። አስፈልጎኝ የነበረ ነገር በሙሉ በእሱ ነው የተገኘው። ወደ ሌላ መሄድ እንዴት ልፈልግ እችላለው?

145 ወንድም፡ እህቶች ሆይ፡ ዛሬ ወደዚህ ምንጭ አትመጡምን? አትመጡምን፡ በዚያም ገብታችሁ የማታውቁ ከሆናችሁ፡ ዛሬ አንገቶቻችንን ዝቅ አድርገን እያለን አትቀበሉምን?

146 የተቀደዱ ጉድጓዶች፡ የሚያፈሱ፡ የሚያንጠባጥቡ፡ አለም ወደሱ የሚፈስ፡ የሌላ ቀናት ጉሮኖ ቆሻሻ የሚጠራቀምበት። እንዲህ ያሉ ነገሮች የማይገቡበት፡ ይህ ምንጭ አይሻልም ወይ፡ በደም የተሞላ ታላቅ ምንጭ፡ ከአማኑኤል የደም ስሮች የተቀዳ ምንጭ ጋር አትመጡምን? ለምን ዛሬ አትቀበሉምን? ዛሬ፡ በዚህ በደረቅ እና በተጠማ ምድር፡ እግዚአብሔር ይርዳን። ነብዩ እንዳለው፡ “በዝለት ምድር ውስጥ አለት ነው።” ያን ምንጭ እርሱ ነው። በዛሬ ምሽት፡ እየጸለይን፡ በልባችሁ ወደሱ አትመጡምን?

147 ውድ የሰማይ አባታችን፡ ሌላ ምንም ምንጭ የለም፡ ሙዚቃው እየተጫወተ፡ “ሌላ ምንጭ አላውቅም፡ የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።” በመገኘቱ ውስጥ፡ በዚያው ተወልጃለሁና፡ እዚያው አደኩኝ፡ እዚያው ኖሬ፡ እዚያው መሞት

ፈልጋለው፡ እንደገናም እዚያው መነሳት እፈልጋለሁ። ጌታ ሆይ፡ ሌላ የማውቀው የለኝምና፡ ሁል ጊዜ፡ በመገኘቱ ውስጥ ልሁን። የሃይማኖት መገለጫ ሳይሆን፡ ከክርስቶስ በቀር ሌላ ፍቅር፡ ሌላ ፍቅር የለንም፡ ከክርስቶስ በቀር ሌላ የሐይማኖት መግለጫ የለንም፡ ከመጽሀፍ ቅዱስ በቀር ሌላ መጽሐፍ የለንም። ሌላ ነገር የለንም፡ ከሱ ውጭ ሌላ ደስታ የለንም። እግዚአብሔር ሆይ፡ ምንም ያህል የዓለም ነገር ቢሞላልኝ፡ እነሆ—የሞተ ነውና፡ አቤቱ ውሰድልኝ፡ እጆቼ ከራሴ በላይ ሆነው እንከራተታለሁ። ከእኔ ውሰደው፡ ጌታ ሆይ፡ እኔ እሄዳለው። እሱ ግን በእኔ ውስጥ ይኑር፡ ያኔ ታሕሳስ እንደ ግንቦት ያማረ ይሆናል፡ ያኔ ደረቅ ቦታ እና ሞቃታማ ቦታ አይኖርም፡ ሞት እንኳን አያሸንፈውም። አባት ሆይ፡ እሱ ይኑረን። ለእያንዳንዱ አማኝ፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ላሉት፡ እሱን እንደጠበቁት፡ አትረፍርፈህ ስጣቸው ጌታ ሆይ።

148 ብዙዎቹ ዛሬ ማታ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ በመንገድ ላይ መንዳት ይኖርባቸዋል፡ ወደ ቤታቸው በሚሄዱበት ጊዜ፡ አሳባቸው እንዲህ ይሁን፡ “እነሆ መኖሪያዬ ከምንጩ ስር ነው። ከሰዓት ወደ ሰዓት፡ ፍሬሽ እየጠጣሁ፡ እነሆ መኖሪያዬ በዚያ ነው።”

149 እና እሱን አሁን ካልተቀበሉ፡ አሁን፡ ይቀበሉት፡ ምንጩን ይዘው ይሄዱ ዘንድ አሁን እሱን ያግኙት። “ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ።” አባት ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች አድርጋቸው።

150 አሁንም ራሶቻችንን ዝቅ እንዳልን፡ ዛሬ ምሽት፡ አንድ ሰው ካለ፡ ወይም ሰንቶቻችሁ፡ “ጌታ ሆይ፡ አሁኑኑ ወደዛ ምንጭ ውሰደኝ የምትሉት። እዚህ ቦታ የመጣሁት ለመስማት ብቻ አይደለም፡ የሆነ ነገር ለማግኘት ነው። እዚህ የመጣሁት አንተን ለማግኘት ነው፡ ጌታ ሆይ። ዛሬ ምሽት አንተ ታስፈልገኛለህ። አሁን ወደ ልቤ ግባ። ጌታ ሆይ፡ ፈቃድህ ነውን? ” እግዚአብሔር ይባርክህ። እያንዳንዳችሁን ጌታ ይባርካችሁ።

151 አባት ሆይ፡ እነዚህን እጆች አይተሃቸዋል፡ እላይ ያሉትን እና በግድግዳው ዙሪያ ያሉትንም፡ እና በሌሎች ክፍሎች ያሉትን፡ ውጭ ያሉትንም አይተሃቸዋል ጌታ ሆይ። አባት ሆይ፡ አንተ—አንተ አይተሃቸዋል። የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንድትሰጣቸው እ—እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ምናልባት የሆነ ሰው በግምሽ-መንገድ ብቻ ጉድጓድ በቆፈረበት፡ ከአሮጌ ጉድጓዶች ሲጠጡ ቆይተው ሊሆን ይችላል፡ በሁሉም ዓይነት እንግዳ አስተምህሮዎች፡ ቃሉን በመካድ ተበክለው ይሆናል። እግዚአብሔር፡ ዛሬ ምሽት ምንጭ ወደ ሆነው፡ ወደ ሕይወት ምንጭ፡ ወደሱ እንዲመጡ እጸልያለሁ። አድርገው፡ አባት ሆይ። አሁን በኢየሱስ ስም እነሱን ለአንተ አደራ እሰጣለሁ።

152 አንተም “በስሜ ምንም ነገር ብትጠይቀኝ፡ ይሆንልሃል፡” ብለኸኛልና። ጌታ ሆይ፡ አሁን፡ እንደምታደርገው ባላምን ኖሮ፡ አልጠይቅህም ነበር። በተለመደው የአምልኮ ሰርዓት ብቻ—ነበር የምለው። ስለ እነሱ ግን፡ በቅንነት እጸልያለሁ። የገባኸውን ቃል፡ እንደምትፈጽም በማመን እጸልይላቸዋለው።

153 እና አሁን ዛሬ ማታ ከዚያ ጉድጓድ ውስጥ እወስዳቸዋለሁ። ከዚህ በፊት ይጠጡ ከነበረበት ቦታ እወስዳቸዋለሁ፡ ከዚያ እርካታ ከሌለበት፤ ወደ ምንጩ እወስዳቸዋለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አደርገዋለሁ።

154 ጌታ ሆይ፡ የአንተ ናቸው። ከአንተ ይጠጡ፡ ሕያው ውሃ፡ የሕይወት ውኃ ምንጭ። በኢየሱስ ስም፡ እጠይቃለሁ። አሜን። አድርገው፡ ጌታ ሆይ።

ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ፡
ኃጢአቴን ያጠበው፡
ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

ኃጥያቴን ማን ያጥበዋል?
የ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው፤
ማን ንጹህ ያደርገኛል?
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።
ኦህ...

ኢየሱስ፡ እነዚህን ፈዉሳቸው፡ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ፡ በኢየሱስ ስም፡ አድርገው። እግዚአብሔር ሆይ፡ አንተን... ? ... እለምንሃለሁ፡ አንተ ሁሉን ታውቃለህ።

ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
ኦህ፡ የክርስቶስ ደም ብቻ ነው...

155 አሰቡት፡ ሌላ ምንጭ አላውቅም! ከእርሱ በቀር ሌላ አላውቅም። ከእርሱ በቀር ሌላ ነገር የማወቅ ፍላጎት የለኝም። ከኢየሱስ ደም በቀር ምንም! ኦህ!

ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ፡
ኃጢአቴን ያጠበው፤
ሌላ ምንጭ አለውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

156 ያን በድጋሚ እየዘመርን፡ እርስ በእርሳችን ሰላም እንባባል። እርስ በርሳችሁ ትዋደዳላችሁ? እዚህ ቦታ ላይ በሌላ ሰው ላይ አንዳች ነገር ያለበት ሰው አለ? ካለ፡ ሂዱና አስተካክሉት። ፈቃደኞች ናችሁ? ከዚህ ቦታ እንዲሁ አንውጣ። አያችሁ? በማንም ላይ አንዳች ነገር ካላችሁ፡ አሁኑኑ፡ ሂዱና አስተካክሉት። አሁን የመሄድ እድላችሁ ነው፡ ሂዱና፡ "ወንድሜ፡ እህቴ፡ ሰላንተ የሆነ ነገር ብያለሁ፡ የሆነ ነገር አሰብያለሁ። እንደሱ ለማድረግ ፈልጌ አልነበረም። ይቅርታ አድርግልኝ።" አያችሁ፡ እንደሱ ነው የሚደረገው። ሁል ጊዜ፡ ምንጩ በመካከላችን ይሁንልን። አያችሁ?

ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ፡
ኃጢአቴን ያጠበው፤
ኦህ፡ ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

157 ኦህ፡ እሱ አይደንቅም ወይ? ሌላ ምንጭ የለም! ራሳችንን በሌሎች ነገሮች አንበክልም። ተለይተናል፡ አለምን ወደ ኋላ ትተናል። ከእንግዲህ የግብፅ ሽንኩርት እና የተቀደዱ ጉድጓዶች አንፈልግም። ከጌታ ኢየሱስ ጋር እንጓዛለን፡ ያ

የተመታው ዓለት፡ አሜን፡ ከላይ መና እየተመገብን፡ እና እየጠጣን፣ የመላዕክትን ምግብ እየበላን፡ እና ከዓለቱ እየጠጣን። አሜን!

ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

አሁን አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

158 እግዚአብሔር እያንዳንዳችሁን አብዝቶ እንዲባርክ እጸልያለሁ፡ ፀጋው እና ምህረቱ በመጪው ሳምንት ከእናንተ ጋር ይሆናል። ምናልባት አንድ ነገር እንኳ ቢከሰት፡ ምናልባት ከእናንተ አንዱ አሁን በሞት ሊወሰድ ይችላልና፡ ተኝተን አርፈን እስክንገናኝ ድረስ ያለው ሰዓታት እጅግ ጥቂት እንደሆኑ አትርሱ። አስታውሱ፡ ማለት፡ "ህያዋን ሆነን የምንቀር ተኝተው ያሉትን አንቀድምም፡ የእግዚአብሔር መለከት፡ የመጨረሻው መለከት… " ስድስተኛው አሁን ተሰምተዋል። የመጨረሻው መለከት፡ ልክ እንደ መጨረሻው ማህተም፡ የጌታ መምጣት እሱ ይሆናል። "የመለከት ድምጽ ይሰማል፡ እናም በክርስቶስ የሞቱት ቀድመው ይነሳሉ።" እስከዚያ ድረስ እረፍት ብቻ ያደርጋሉ።

159 ምናልባትም ብትጎዱ፡ ይህን አስታውሱ፡

የኢየሱስን ስም ከአንተ ጋር ይሂድ፡
ከወጥመድ ሁሉ እንደ ጋሻ፡
ዙራህ ሁሉ ፈተና ሲበዛ፡
ያን ቅዱስ ስም በፀሎት ጥራ። (አጋንንት ይሸሻሉ።)

160 ብቻ አስታውሱ፡ በሚቀጥለው እሁድ ማለዳ እዚህ እንደምንገናኝ ተስፋ እናደርጋለን። የታመሙትን እና የተቸገሩትን ወደዚህ አምጡ። እጸልይላችኋለሁ። አሁን ትጸልዩልኛላችሁ። ታደርጋላችሁ? "አሜን።" በሉ፡ [ጉባኤው፡ "አሜን።" አለ—እርታዒ።] እግዚአብሔር እንድባርካችሁ፡ እጸልይላችኋለሁ።

… ስሙን በፀሎት።

ድንቅ ስም፡ (የተከበረ ስም!) ኡህ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

ለኢየሱስ ስም ስገዱ፣
በእግሩ ስር ተደፍታችሁ፡
የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ያጠልቃል፡
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

የተከበረ ስም፡ (የተከበረ ስም! ጣፋጭና የተከበረ አይደለም? )
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ (የተከበረ ስም!) ኡ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

161 ሁል ጊዜ ከእናንተን መለየት በጣም ከባድ ነው። ጊዜዬ እያለቀ እንደሆነ አውቃለሁ፡ ግን ብቻ የሆነ ነገር አለ… እስቲ፡ የሆነ አንድ ጥቅስ ብቻ፡

ታደርጉታላችሁ? [ጉባኤው፡ “አሜን።” አለ—አርታዒ።] ታደርጉታላችሁ? **ብለሰት ቢ ዘ ታይ ዛት ባይንድስ፡** እህቴ። ሰንቶቻችሁ የድሮውን መዝሙር ታውቃላችሁ? ከዓመታት በፊት፡ ሰንዘምር የነበርነውን።

162 እኔም ዛሬ ምሽት፡ እያሰብኩት ነበር፡ “ከመተዎቹ፡ ሁለት እጆች፡ ቀርተዋል፡” በመገናኛ ድንኳን ዙሪያ ያን መዝሙር ሰንዘምር፡ እና እጅ ለእጅ ሰንያያዝ። **ብለሰት ቢ ዘ ታይ ዛት ባይንድስ።** ብዙዎችን፡ እዚያው መቃብር ውስጥ ቀብርያቸዋለሁ። ይጠባበቃሉና። እንደገና ኢያቸዋለሁ። ከአድማሰ ማዶ ሰመለከት፡ አንድ ጊዜ፡ በራዕይ፡ አይቻቸዋለሁ። እዚያ አሉ።

አሁን እየዘመርን ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

> በክርሰቶሰ ፍቅር ልባችንን
> ያሰረ ማሰሪያ የተባረከ ይሁን፡
> ህብረቱ...
> ደሰ ይላል ከላይ ያለውን።
>
> እኛም...

አሁን ጠጋ ብለን የአንድን ሰው እጅ እንያዝ።

> ... የተቋረጠ ክፍል፡

አሁን ራሶቻችሁን ዝቅ አድርጉ።

> ውሰጣችን ቢያንም እንኳ፤
> በልባችን ግን አንድ እንሆናለን፡
> በድጋሚ እንድንገናኝ ተሰፋ እናደርጋለን።

163 ራሶቻችንን ዝቅ እንዳደረግን። መድረኩን ለፓሰተር እሰጥና፡ ይጨርሳል...

64-0726E የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው ።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org